# የቤተሰብ

መምሪያ መጽሐፍ

# የቤተሰብ

መመሪያ መፅሐፍ

አሳታሚው
የኋላኛው፡ ቀን፡ ቅዱሳን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ቤተክርስትያን
ሶልት፡ ሌክ፣ ዩታ

© 1992, 1999, 2001, 2006 by Intellectual Reserve, Inc
የባለቤቱ፡ መብት፡ የተጠበቀ፡ ነው
በዩ ኤስ ኤ ውስጥ፡ ታተመ

English approval: 2/06
Translation approval: 2/06
Translation of *Family Guidebook*
Amharic

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| “ቤተሰብ፤ ለአለም፡ የተላለፈ፡ አዋጅ” | iv |
| የቤተሰብ፡ አደረጃጀት፡ እና፡ አላማ | ፩ |
| በቤት፡ ውስጥ፡ ወንጌልን፡ ማስተማር | ፬ |
| የቤተሰብ፡ ሀላፊነትን፡ ማሟላት | ፲፪ |
| የመሪነት፡ ስልጠና | ፲፫ |
| በቤት፡ ውስጥ፡ ለአምልኮት፡ ስርዓት፡ መሰብሰብ (በተነጠለ፡ ቦታ፡ ለሚኖሩ፡ ቤተሰቦች) | ፲፯ |
| የክህነት፡ ስርዓቶች፡ እና፡ በረከቶች | ፲፰ |
| የቤተክርስትያን፡ እቃዎችን፡ እና፡ ስለቤተሰብ፡ ታሪክ፡ መረጃዎችን፡ ማግኘት | ፳፯ |

# “ቤተሰብ፡ ለአለም፡ የተላለፈ፡ አዋጅ”

በ1995፡ ዓ/ም፣ የቀዳሚ፡ አመራር፡ እና፡ የአስራ፡ ሁለቱ፡ ሀዋሪያት፡ ቡድን፡ ይህን፡ “ቤተሰብ፡ ለአለም፡ የተላለፈ፡ አዋጅ” የሚለውን፡ አወጡ። ይህ፡ አወጅ፡ በቤተክርስትያኑ፡ ታሪክ፡ ውስጥ፡ በሙሉ፡ የነበሩት፡ ነብያት፡ በተደጋጋሚ፡ የገለጹትን፡ ትምህርቶች፡ እና፡ ልምዶችን፡ የሚገልፅ፡ እና፡ የሚያረጋግጥ፡ ነው። ይህም፡ ለእያንዳንዱ፡ ቤተሰብ፡ ደስታ፡ እና፡ ደህንነት፡ ጠቃሚ፡ የሆኑ፡ መሰረቶችን፡ ይዟል። ይህን፡ አዋጅ፡ የቤተሰብ፡ አባሎች፡ ሊያጠኑት፡ እና፡ በህግጋቱም፡ ሊኖሩ፡ ይገባል።

---

“እኛ፡ የኋለኛው፧ ቀን፡ ቅዱሳን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ቤተክርስትያን፡ ቀዳሚ፡ አመራር፡ እና፡ የአስራ፡ ሁልቱ፡ ሐዋርያት፡ ሸንጎ፡ በእርጋታ፡ በወንድ፡ እና፡ በሴት፡ መካከል፡ ያለ፡ ጋብቻ፡ የእግዚአብሔር፡ ስርዓት፡ እንደሆነ፡ እና፡ ቤተሰብም፡ ፈጣሪው፡ ለልጆቹ፡ ላለው፡ ዘላለማዊ፡ እጣ፡ አላማ፡ ዋና፡ ክፍል፡ እንደሆነም፡ እንገልጻለን።

“የሰው፡ ልጆች፡ በሙሉ—ወንድና፡ ሴቶች፡—በእግዚአብሔር፡ አምሳል፡ ነው፡ የተፈጠሩት። እያንዳንዱም፡ የሰማይ፡ ወላጆች፡ የተወደዱ፡ የመንፈስ፡ ሴት፡ እና፡ ወንድ፡ ልጆች፡ ናቸው፣ እናም፡ ይህ፡ ስለሆኑም፣ እያንዳንዱ፡ መለኮታዊ፡ ተፈጥሮ፡ እና፡ ፍጻሜም፡ አላቸው። ጾታም፡ አስፈላጊ፡ የሆነ፡ የግለሰብ፡ ቅድመ፡ ምድራዊ፣ ሟች፣ እና፡ ዘለአለማዊ፡ መለያ፡ እና፡ አላማ፡ እና፡ ባህሪ፡ ነው።

“በቅድመ፡ ምድራዊ፡ ህይወት፡ ውስጥ፣ የመንፈስ፡ ወንድ፡ እና፡ ሴት፡ ልጆች፡ እግዚአብሔርን፡ እንደ፡ ዘላለማዊ፡ አባታቸው፡ ያውቁትም፡ ያመልኩትም፡ ነበር፣ እናም፡ ልጆቹ፡ ስጋዊ፡ አካልን፡ አግኝተው፡ ምድራዊ፡ አጋጣሚዎችን፡ በማግኘት፡ ወደፍጹምነት፡ ለመሻሻል፡ እና፡ በመጨረሻም፡ እርሱ፡ ወይም፡ እርሷ፡ እንደ፡ መለኮታዊ፡ እጣቸው፡ ዘላለማዊ፡ ህይወትን፡ ወራሽ፡ እንዲሆኑ፡ የሚያደርገውን፡ አላማውን፡ ተቀብለው፡ ነበር። መለኮታዊው፡ የደስታ፡ እቅድ፡ የቤትሰብ፡ ግንኙነት፡ ከመቃብር፡ ባሻገር፡ እንዲቀጥልም፡ ያስችላል። በቅዱስ፡ ቤተ፡ መቅደሶች፡ የሚገኙትም፡ ቅዱስ፡ ስነ፡ ስርዓቶች፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳኖችም፡ ግለሰቦች፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ፊት፡ ለመመለስ፡ እና፡ ቤተሰቦችም፡ ለዘላለም፡ እንዲጣመሩ፡ ያስችላቸዋል።

“እግዚአብሔር፡ ለአዳም፡ እና፡ ለሔዋን፡ የሰጠው፡ የመጀመሪያው፡ ትእዛዝ፡ እንደባልና፡ ሚስት፡ ስላላቸው፡ የወላጅነት፡ አቅም፡ ነበር። እግዚአብሔር፡ ልጆቹን፡ እንዲባዙ፡ እና፡ ምድርን፡ እንዲሞሉ፡ ዘንድ፡ የተሰጠው፡ ትእዛዝ፡ አሁንም፡ ተግባራዊ፡ ነው፡ ብለን፡ እናውጃለን። የተቀደሱት፡ የመዋለድ፡ ሀይሎች፡ እንደ፡ ባልና፡ ሚስት፡ በህግ፡ በተጋቡት፡ ወንዶች፡ እና፡ ሴቶች፡ መካከል፡ ብቻ፡ መፈጸም፡ እንዳለበትም፡ እግዚአብሔር፡ እንዳዘ፡ ጨምረንም፡ እናውጃለን።

“ሟች፡ ህይወትን፡ የሚፈጠሩት፡ መንገድም፡ በመለኮታዊ፡ እንደተወሰኑ፡ እንደሆኑም፡ እንገልጻለን። የህይወትን፡ ቅድስና፡ እና፡ በእግዚአብሔር፡ ዘላለማዊ፡ እቅድ፡ ውስጥ፡ ያለውን፡ አስፈላጊነትንም፡ እናረጋግጣለን።

“ባል፡ እና፡ ሚስት፡ እርስ፡ በራሳቸው፡ እና፡ ከልጆቻቸው፡ ጋር፡ ለመፈቃቀር፡ እና፡ ለመንከባከብ፡ ሀላፊነት፡ አለባቸው። ‘ልጆች፡ የጌታ፡ ወራሽ፡ ናቸው።’ (መዝሙር 127፤3) ወላጆች፡ ልጆቻቸውን፡ በፍቅር፡ እና፡ በጻድቅነት፡ የማሳደግ፣ እናም፡ የስጋዊ፡ እና፡ የመንፈሳዊ፡ ፍላጎታቸውን፡ የማሟላት፣ እርስ፡ በራስ፡ እንዲዋደዱ፡ እና፡ እንዲያገለግሉ፣ የእግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡ እንዲያከብሩ፡ እና፡ በሚኖሩበት፡ ቦታ፡ ህግ፡ አክባሪ፡ ዜጎች፡ እንዲሆኑ፡ የማስተማር፡ ሀላፊነት፡ አለባቸው። ባሎች፡ እና፡ ሚስቶችም፣ እንዲሁም፡ እናቶች፡ እና፡ አባቶች፣ ለእነዚህ፡ ሀላፊንቶች፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ተጠያቂዎች፡ ይሆናሉ።

“ቤተሰብ፡ በእግዚአብሔር፡ የተሰጠ፡ ነው። በወንዶች፡ እና፡ ሴቶች፡ መካከል፡ ያለ፡ ጋብቻም፡ ለዘላለማዊ፡ እቅድ፡ ውስጥ፡ በጣም፡ አስፈላጊው፡ ነው። ልጆችም፡ በጋብቻ፡ ጥምረቶች፡ ውስጥ፡ የመውለድ፣ እናም፡ የጋብቻ፡ ቃል፡ ኪዳናቸውን፡ በሙሉ፡ ታማኝነት፡ በሚያከብሩ፡ አባት፡ እና፡ አናት፡ የማደግ፡ መብት፡ አላቸው። በቤተሰብ፡ ህይወት፡ ውስጥ፡ ደስታ፡ የሚገኘው፡ ቤተሰብ፡ በጌታ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ትምህርት፡ በኩል፡ ሲገነባ፡ ነው። የተሳኩ፡ ጋብቻዎች፡ እና፡ ቤተሰቦች፡ የሚመሰረቱት፡ እና፡ የሚጸኑት፡ በእምነት፣ በጸሎት፣ ንስሀ፡ በመግባት፣ በምህረት፣ በክብር፣ በፍቅር፣ በርህራሄ፣ በስራ፣ እና፡ በመልካም፡ መዝናኛ፡ እንቅስቃሴዎች፡ መሰረት፡ በኩል፡ ነው። በመለኮታዊ፡ እቅድ፣ አባቶች፡ በፍቅር፡ እና፡ በጻድቅነት፡ ቤተሰቦቻቸውን፡ ያስተዳድራሉ፡ እና፡ ለቤተሰቦቻቸው፡ የህይወት፡ መሰረታዊ፡ ፍላጎት፡ የሟሟላት፡ እና፡ ጥበቃ፡ ሀላፊነት፡ አለባቸው። እናቶች፡ በቀደምትነት፡ ልጆቻቸውን፡ የመንከባከብ፡ ሀላፊነት፡ አለባቸው። በእነዚህ፡ ቅዱስ፡ ሀላፊነቶችም፣ አባቶች፡ እና፡ እናቶች፡ በእኩል፡ አጋርነታቸው፡ የመረዳዳት፡ ሀላፊነት፡ አለባቸው። በአካል፡ ጉዳት፣ በሞት፣ ወይም፡ በሌሎች፡ ሁኔታዎች፡ ምክንያትም፡ እነዚህን፡ ሀላፊነቶችን፡ ማመጣጠን፡ ያስፈልጋል። ለቅርብ፡ዘመዶችና ቤተሰቦችም፡ አስፈላጊ፡ ሲሆን፡ እርዳታ፡ መስጠት፡ ይገባቸዋል።

“የንፅህና፡ ቃል፡ ኪዳንን፡ የሚሰብሩ፣ ባለቤቶቻቸውን፡ ወይም፡ ልጅቻቸውን፡ የሚበድሉ፣ ወይም፡ የቤተሰብ፡ ሀላፊነታቸውን፡ የማያከናውኑ፡ ሁሉ፡ አንድ፡ ቀን፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ በተጠያቂነት፡ እንድሚቆሙም፡ እናስጠነቅቃቸዋለን። በተጨማሪም፣ የቤተሰብ፡ መፈራረስ፡ በግለሰብ፣ በህብረተሰብ፣ እናም፡ በአገሮች፡ ላይ፡ በጥንት፡ እና፡ በዘመኑ፡ ቀድመው፡ የተነገሩት፡ ጥፋቶች፡ እንደሚመጡባቸውም፡ እናስጠነቅቃለን።

በየትም፡ ስፍራ፡ ላሉት፡ ሀላፊነት፡ ላላቸው፡ ዜጎች፡ እና፡ የመንግስት፡ ባለስልጣኖች፡ ቤተሰብ፡ የማህብረሰብ፡ ዋና፡ መሰረታዊ፡ ክፍል፡ እንዲሆን፡ እና፡ እንዲጠናከር፡ እርምጃዎች፡ እንዲወስዱም፡ ጥሪ፡ እናቀርባለን።” (*Ensign,* ህዳር፡ **1995, 102)**

# የቤተሰብ፡ አደረጃጀት፡ እና፡ አላማ



## አደረጃጀት

በኋለኛው፡ ቀን፡ ቅዱሳን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ቤተክርስትያን፡ ውስጥ፡ ቤተሰብ፡ የተቀደሰ፡ ነው፡ እናም፡ በጊዜያዊ፡ እና፡በዘላለም፡ ውስጥ፡ በጣም፡ አስፈላጊ፡ ማህብራዊ፡ ክፍል፡ ነው። እግዚአብሔር፡ ቤተሰብን፡ የመሰረተው፡ ለልጆቹ፡ ደስታን፡ ለማምጣት፣ ትክክለኛ፡ ትምህርትን፡ ፍቅር፡ በሞላበት፡ ስፍራ፡ እንዲማሩ፣ እና፡ ለዘለአለማዊ፡ ህይወት፡ እንዲዘጋጁ፡ ለማድረግ፡ ነው።



ቤትም፡ ለመማርና፣ለማስተማር፣ እና፡ የወንጌልን፡ መሰረት፡ ለመተግበር፡ ትክክለኛው፡ ቦታ፡ ነው። እነዚህም፡ ግለሰቦች፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ እናም፡ ሌሎች፡ አስፈላጊ፡ ነገሮችን፡ ለማግኘት፡ የሚማሩበት፡ ቦታ፡ ነው። አባትና፡ እናት፡ በእኩል፡ ተባባሪነት፡ እያንዳንዱን፡ የቤተሰብ፡ አባላት፡ የሚቀጥሉትን፡ እንዲያደርጉ፡ መርዳት፡ አለባቸው፧

- እውነትን፡ እንዲፈልጉ፡ እና፡ በእግዚአብሔር፡ እምነት፡ እንዲጎለብቱ።

- ለኃጥያት፡ ንስሀ፡ እንዲገቡ፣ ለኃጥያት፡ መሰረይ፡ እንዲጠመቁ፣ የኋለኛው፡ ቀን፡ ቅዱሳን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ቤተክርስትያን፡ አባል፡ እንዲሆኑ፣ እና፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ እንዲቀበሉ።
- የእግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡ እንዲያከብሩ፣ ቅዱስ፡ መጻህፍትን፡ በትጋት፡ እንዲያጠኑ፣ በየቀኑም፡ የግል፡ ጸሎትን፡ እንዲያቀርቡ፣ እና፡ ሌሎችን፡ እንዲያገለግሉ፡ መርዳት።
- ወንጌልን፡ ከሌሎች፡ ጋር፡ እንዲካፈሉ።
- የቤተመቅደስ፡ መንፈሳዊ፡ ስጦታን፡ እንዲቀበሉና፡ ከብቁ፡ የትዳር፡ ጓደኛ፡ ጋር፡ በቤተመቅደስ፡ እንዲጋቡ፣ ደስተኛ፡ ቤትም፡ ለቤተሰቦቻቸው፡ እንዲሰሩ፣ እናም፡ ቤተሰብን፡ በፍቅርና፡ በመስዋዕት፡ እንዲደግፉ።



- ሞተው፡ ስላለፉት፡ ዘሮቻቸው፡ መረጃ፡ እንዲመረምሩ፡ እና፡ የቤተመቅደስ፡ ስነ፡ ስርዓቶችን፡ ለእነርሱ፡ እንዲያከናውኑ።
- ለመንፈሳዊ፣ ለማህብረሰባዊ፣ ስጋዊ፣ እና፡ ስሜታዊ፡ ጤንነት፡ የሚያስፈልገውን፡ እንክብካቤ፡ እንዲያሟሉ።

አባት፡ ቤተሰብን፡ ይመራል፡ እናም፡ ልጆችን፡ የማስተማር፡ እና፡ ለህይወት፡ አስፈላጊ፡



ነገሮችን፡ የማቅረብ፡ ሀላፊነት፡ አለበት። በቤተክርስትያን፡ ውስጥ፡ ብቁ፡ የሆነው፡ እና፡ ተገቢው፡ አባት፣ በእግዚአብሔር፡ ስም፡ የማገልገል፡ ሀይልና፡ ስልጣን፡ የሆነውን፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ ለመያዝ፡ እድል፡ ይኖረዋል። በዚህ፡ ስልጣን፡ እና፡ ሐይል፣ አባት፡ የቤተሰቡ፡ የክህነት፡ መሪ፡ ይሆናል። ወደሰማይ፡ አባት፡ ለመመለስ፡ በሚያደርጉት፡ ዝግጅትም፡ ቤተሰቡንም፡ ይመራል። ባለቤቱም፡ ዋናዋ፡ ጓደኛ፣ አጋር፣ እና፡ አማካሪ፡ ናት። ባልና፡ ሚስት፡ ቤተሰባቸውን፡ እና፡ ቤታቸውን፡ በሚነኩ፡ ጉዳዮች፡ ሁሉ፡ መመካከር፡ ይገባቸዋል።

አባት፡ የቤተሰቡን፡ መንፈሳዊ፡ ፍላጎት፡ ማሟላት፡ አለበት። የኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ወንጌል፡ መማራቸውን፡ እና፡ የጌታን፡ ትእዛዝ፡ እንዲያከብሩ፡ ለማበረታታት፡ እና፡ ለመርዳት፡ የሚቻለውን፡ ሁሉ፡ ማድረግ፡ ይገባዋል።

የክህነት፤ ስልጣንን፡ የያዘ፡ አባት፡ ቤተሰቡን፡ ለመባረክ፡ እና፡ የመንፈሳዊ፡ ፍላጎታቸውን፡ ለማሟላት፡ ይችላል። አግባብ፡ ባለው፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ እና፡ በክህነት፡ ስልጣን፡ መሪዎች፡ ትዕዛዝ፣ አባት፡ የሚከተሉትን፡ ማድረግ፡ ይችላል፣

፩ ለልጆቹ፡ ስም፡ ማውጣትና፡ መባረክ።

፪ ልጆቹን፡ (እናም፡ ሌሎችን) ማጥመቅ።

፫ ልጆቹን፡ (እና፡ ሌሎችን፡) የቤተክርስትያን፡ አባልነታቸውን፡ ማረጋገጥ፡ እና፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ መስጠት።

፬ ለወንድ፡ ልጆቹ፡ (እና፡ ለሌሎችም፡) የክህነት፡ ስልጣን፡ መስጠት፡ እና፡ በክህነት፡ ስልጣን፡ ውስጥ፡ ወዳሉት፡ ሀላፊነቶችም፡ መሾም።

፭ ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ መባረክ፡ እና፡ ማስተላለፍ።

፮ መቃብሮችን፡ መባረክ።

ከእርሱ፡ የክህነት፡ መሪዎች፡ ትዕዛዝ፡ ውጪም፥ የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ የያዘ፡ አባት፡ ቅባቅዱስ፡ዘይት፡ የመቀደስ፡ እና፡ ሲታመሙም፡ ቤተሰቡንና፡ ሌሎችን፡ የመባረክ፡ እና፡ በሚያስፈልጋቸው፡ ጊዜም፡ ልዩ፡ በረከቶች፡ በሌሎች፡ ጊዜያት፡ መስጠት፡ ይችላል። (የክህነት፡ ስልጣን፡ ስነ፡ ስርዓቶችን፡ እና፡ በረከቶችን፡ ለመፈጸም፡ የተሰጡትን፡ መመሪያዎች፡ በዚህ፡ መመሪያ፡ መፅሐፍ፡ ውስጥ፡ በገፅ፡ 15–25፡ ላይ፡ ይመልከቱ።)

አባት፡ ቤተሰቡን፡ የሚቀጥሉትን፡ ሶስት፡ ሀላፊነቶች፡ በንቃት፡ እንዲሳተፉ፡ ማድረግ፡ አለበት፡

፩ የግል፡ እና፡ የቤተሰብ፡ መንፈሳዊ፡ እና፡ ስጋዊ፡ ዝግጁነት።

፪ ወንጌልን፡ መካፈል።

፫ የቤተሰብ፡ ታሪክ፡ መፈለግ፡ እና፡ የቤተመቅደስ፡ ስርዓቶችን፡ በህይወት፡ ላሉት፧ እና፡ ለሞቱት፡ ማከናወን።

እናት፡ ለባለቤቷ፡ እኩል፡ አጋር፡ እና፡ አማካሪ፡ ነች። የእግዚአብሔር፡ ህግጋት፡ ልጆቻቸውን፡ ለማስተማር፡ ታግዘዋለች። በቤት፡ ውስጥ፡ አባት፡ ከሌለም፥ እናት፡ የቤተሰቡ፡ መሪ፡ ናት።

አባት፡ እና፡ እናት፡ በአላማ፡ አንድ፡ መሆን፡ አለባቸው። ግባቸውም፡ የቤተሰብ፡ አባላትን፡ በሙሉ፡ ወደሰማዩ፡ አባታችን፡ ይመለሱ፡ ዘንድ፡ ለማዘጋጀት፡ መሆን፡ አለበት። ጌታ፡ ቤተክርስትያኑን፡ ያቋቋመው፡ አባት፡ እና፡ እናት፡ ልጆቻቸውን፡ እንዲያስተምሩ፡ እና፡ እንዲንከባከቡ፡ ለመርዳት፡ ነው።

ልጆች፡ ወደ፡ ቤተሰብ፡ ሲመጡ፥ ወላጆች፡ ሊያፈቅሯቸው፥ የወንጌሉን፡ እውነት፡ ሊያስተምሯቸው፥ እና፡ የጻድቅ፡ አኗኗር፡ ምሳሌዎች፡ ሊሆኗቸው፡ ይገባል። ልጆች፡ የእግዚአብሔርን፡ ትዕዛዝ፡ መማር፡ እና፡ መጠበቅ፡ አለባቸው። እነርሱም፡ ወላጆቻቸውን፡ ማክበር፡ እና፡ ሊታዘዙም፡ ይገባቸዋል።

የቤተክርስትያኑ፡ ጥንካሬ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወንጌል፡ በሚኖሩት፡ ቤተሰቦች፡ እና፡ ግለሰቦች፡ ላይ፡ ይመካል። አባት፡ እና፡ እናት፡ የወላጅነት፡ መሰረታዊ፡ ተግባሯቸውን፡ መረዳታቸውና፡ ማከናወናቸው፡ የወንጌሉን፡ በረከቶች፡ እንዴት፡ ቤተሰብ፡ እንደሚደሰቱበት፡ ይወስናል። ለአባቶች፡ እና፡ እናቶች፡ የሚጫናቸው፡ ወይም፡ ተስፋ፡ የሚያስቆርጣቸው፡ ወይም፡ መሰረታዊ፡ ሀላፊነታቸውን፡ ችላ፡ የሚያስደርጋቸው፡ ፕሮግራሞች፡ ወይም፡ ሀላፊነቶች፡ በቤተክርስትያን፡ በፍጹም፡ አይሰጣቸውም።

## አላማ

የሰማዩ፡ አባታችን፡ ስለሚወደን፣ እንደእርሱ፡ ከፍ፡ እንድንል፡ ይመኛል። እኛን፡ ለመርዳትም፣ በመለኮታዊ፡ እውነት፡ ህግጋት፡ ላይ፡ የተመሰረተ፡ እቅድ፡ እንድንከተል፡ ሰጥቶናል። ይህን፡ እቅድ፡ በእምነት፡ የሚማሩ፡ እና፡ የሚከተሉም፡ አንድ፡ ቀን፡ እንደ፡ ሰማዩ፡ አባታችን፡ ሆነው፡ የእርሱ፡ አይነት፡ ህይወት፡ ለመኖር፡ ይችላሉ።

ከሰማይ፡ ወደ፡ ምድር፡ መምጣታችንም፡ የእቅዱ፡ አንድ፡ ክፍል፡ ነበር። እዚህ፡ ስጋዊ፡ አካላትን፡ እናገኛለን፣ በአጋጣሚዎቻችን፡ እንማራለን፣ እናም፡ በእግዚአብሐር፤ ፊት፡ ደግመን፡ ለመኖርም፡ ብቁ፡ መሆናችንንም፡ እናረጋግጣለን። ብቁ፡ መሆናችንን፡ የምናረጋግጠውም፡ የእርሱን፡ ህግጋት፡ ለማክበር፡ በነጻ፡ በመምረጥ፡ ነው። (አብርሀም 3፥23–25፤ 2 ኒፋይ 2፡27ን፡ ተመልከቱ።)

ከእርሱ፡ ጋር፡ ለመኖር፡ እንድንዘጋጅ፡ ለመርዳት፣ የሰማዩ፡ አባታችን፡ እኛን፡ በቤተሰብ፡ አደራጅቶናል። በቅዱስ፡ ስነ፡ ስርዓቶች፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳኖች፣ ከቤተሰቦቻችን፡ ጋር፡ ለዘላለም፡ እንኖራለን።

# በቤት፡ ውስጥ፡ ወንጌልን፡ ማስተማር



## ልጆችን፡ በርህራሔ፡ እና፡ ፍቅር፡ ማስተማር

ወላጆች፡ ልጆቻቸውን፡ ወጌልን፡ እንዲያስተምሩ፡ ጌታ፡ አዟቸዋል። እንዲህም፡ ብሏል፤

“ወልጆች፡ በፅዮን፡ ወይም፡ በተደራጁት፡ ስቴኮቿ፡ ውስጥ፡ ልጆች፡ እያላቸው፡ እና፡ የንስሀ፡ መግባትን፡ ትምህርት፣ በህያው፡ እግዚአብሔር፡ ልጅ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እምነት፣ ስምነት፡ አመት፡ ሲሆናቸው፡ ስለ፡ ጥምቀትና፡ እጆችን፡ በመጫን፡ የመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስጦታ፡ እንዲገነዘቡ፡ የማያስተምሩት፣ ኃጥያቱ፡ በወላጆቹ፡ ራስ፡ ላይ፡ ይሆናል።

“ይህም፡ ለፅዮን፡ ወይም፡ ለተደራጁት፡ ማንኛውም፡ ስቴኮቿ፡ ነሪዎች፡ ህግ፡ ነው። “እናም፡ በስምንት፡ አመታቸውም፣ ልጆቻቸው፡ ለኃጥያቶቻቸው፡ ስርየት፡ ይጠመቃሉ፡ እና፡ እጆችን፡ በመጫን፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ይቀበላሉ።

“ልጆቻቸውን፡ እንዲጸልዩ፣ እና፡ በእግዚአብሔር፡ ፊትም፡ በጽድቅ፡ እንዲኖሩም፡ ያስተምሯቸዋል።” (ትምህርትና፡ ቃል፡ ኪዳን 68፥25–28)

ወላጆች፡ ሐዋርያው፡ ጳውሎስ፡ “ በጌታ፡ ምክርና፡ በግሳጼ፡ [ልጆቻቸውን፡] አሳድጓቸው፡” ብሎ፡ የሰጠውን፡ ምክር፡ በማስታወስ፣ በርህራሄ፡ እና፡ ፍቅር፡ አስተምሩ።

## የቤተሰብ፡ ቅዱሳት፡ መፅሐፍት፡ ጥናት

እኛ፡ እንደሰማዩ፡ አባታችን፡ ሆነን፡ የእርሱ፤ አይነት፡ ኑሮ፡ ለመኖር፡ የምንችለው፡ እነዚህ፡ በረከቶች፡ የተመሰረቱበትን፡ ህግጋት፡

በመጠበቅ፡ ብቻ፡ ነው።(ትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን 130፣20–21 ተመልከቱ) በእነዚህ፡ ህግጋት፡ ከመኖራችን፡ በፊት፣ ምን፡ እንደሆኑ፡ ማወቅ፡ አለብን። “ሰው፡ ያለአዋቂነት፡ ለመዳን፡ አይችልም።” (ትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን 131፣6)

ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ መሪያችን፡ እና፡ ህግ፡ ሰጪያችን፡ ነው። መጠበቅ፡ ያለብንን፡ ህጎች፡ እና፡ መንገዶች፡ ያውቃል፣ እናም፡ እያንዳንዳችን፡ እንድንከተለውም፡ ይጋብዛናል። እንዳለው፣ “መንገዱ፡ እኔ፡ ነኝ፤ እውነትና፡ ህይወትም፡ እኔው፡ ነኝ፤ በእኔ፡ በኩል፡ ካልሆነ፡ በቀር፣ ወደ፡ አብ፡ የሚመጣ፡ የለም።” (ዮሀንስ 14፡6) እንደሰማዩ፡ አባታችን፤ ለመሆን፡ እና፡ ወደእርሱ፡ ለመመለስ፣ የኢየሱስን፡ ትምህርቶች፡ መማርና፡ መከተል፡ አለብን። ስለኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ህይወት፣ ትምህርት፣ እና፡ ትእዛዞች፡ ለመማር፡ ይረዱን፡ ዘንድ፡ ቅዱሳት፡ መጻህፍቶች፡ አሉን።

ቤተክርስትያን፡ እንደ፡ ቅዱሳት፡ መጻህፍት፡ የሚቀበላቸው፡ አራቱ፡ ቅዱሳት፡ መፅሐፍት፣ መፅሐፍ ፡ ቅዱስ፣ መፅሐፈ፡ ሞርሞን፣ ትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን፣ እና፡ የዕንቁ፡ ታላቅ፡ ዋጋ፡ መፅሐፍት፡ ናቸው። እነዚህም፡ የወንጌል፡ ህጎችን፡ እና፡ አስተሳሰቦችን፣ ስራዎችን፣ እና፡ ትምህርቶችን፡ የምንመዝንባቸው፡ መስፈርቶችን፡ ይገልጻሉ። ስለኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ህይወት፡ እና፡ ትምህርትም፡ ያስተምሩናል፡ እናም፡ በእግዚአብሔር፡ እምነት፡ ያላቸውን፡ ትእዛዞን፡ ያከበሩት፡ ሰዎችን፡ ምሳሌን፡ ያሳዩናል።

ኢየሱስ፡ ቅዱስ፡ መፅሐፍትን፡ እንድናጠና፡ እና፡ እንድንመረምር፡ አስተምሮናል (ዮሀንስ 5፡39፣ 3ኒፋይ 23፡1፣ ትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን 88፡118ን፡ ተመልከቱ) ።

ቤተሰቦች፡ የጌታን፡ ትምህርት፡ ለመማር፡ እና፡ ለመከተል፡ ቅዱስ፡ መጻህፍትን፡ አብረው፡ በየቀኑ፡ ማጥናት፡ ይገባቸዋል። ወላጆችም፡ በየቀኑ፡ በተመደበ፡ ቀን፡ ቤተሰቦቻቸውን፡ ቅዱስ፡ መጻህፍትን፡ ለማንበብ፡ እና፡ ለመወያየት፡ በአንድነት፡ መሰብሰብ፡ ይገባቸዋል። ማንበብ፡ የሚችሉት፡ እያንዳንዱም፡ የቤተሰብ፡ አባል፡



በቅዱስ፡ መጻህፍቱ፡ የማንበብ፡ እድል፡ እንዲኖራቸውም፡ ያስፈልጋል። ቅዱስ፡ መጻህፍት፡ ከመነበቡ፡ በፊት፣ የቤተሰብ፡ አባልም፡ የሰማዩ፡ አባት፡ እያንዳንዱ፡ በመባረክ፡ የሚነበበውን፡ እንዲረዱ፡ እና፡ ምስክረቱን፡ እንዲያገኙ፡ ዘንድ፡ በጸሎትም፡ ይጠይቁ። ቤተሰቦች፡ ከቅዱስ፡ መጻህፍት፡ ካነበቡ፡ በኋላ፡ የቤተሰብ፡ ጸሎት፡ ለማድረግ፡ ይችላሉ።

ቤተሰቦች፡ ቅዱሳት፡ መጻህፍትን፡ ሲያነቡ፡ እና፡ ሲያስቡባቸው፣ እንደ፡ አዳኝ፡ አይነት፡ ለመሆን፡ ፍላጎት፡ ይኖራቸዋል፡ እናም፡ ታላቅ፡ ደስታና፡ ሰላምም፡ በህይወታቸው፡ ያገኛሉ።

## የግል፡ እና፡ የቤተሰብ፡ ጸሎቶች

እያንዳንዳችን፡ ከሰማዩ፤ አባታችን፤ ጋር፡ በጸሎት፡ ለመነጋገር፡ መማር፡ አለብን። ይወደናል፡ እናም፡ እንድናነጋግረውም፡ ይፈላጋል። ለበረከቶቻችን፡ እንድናመሰግነው፡ እና፡ ለእርሱ፡ እርዳታ፡ እና፡ መሪነት፡ እንድንጠይቀውም፡ ይፈልጋል። ስንጠይቅም፡ ይረዳናል። ብዙዎች፡ ጸሎቶች፡ ተንበርክከን፣ ተቀምጠን፣ ወይም፡ ቆመን፡ ሳለ፡ አንገታችንን፡ በማጎንበስ፡ እና፡ አይኖችን፡ በመጨፈን፡ ነው።

ስንጸልይም፡ አራት፡ አስፈላጊ፡ መሰረቶችን፡ ማስታወስ፡ ያስፈልገናል፡

፩ ጸሎት፡ የምንጀምረው፡ "የሰማይ፡ አባታችን፡ ሆይ . . ." በማለት፡ ወደ፡ ሰማዩ፡ አባታችን፡ እንናገራለን።

፪ ". . . እናመሰግንሀላን፡" በማለትም፡ የሰማዩ፡ አባታችንን፡ ለሰጠን፡ ነገሮች፡ እናመሰግነዋለን።

፫ ". . . እንጠይቅሀላን፡" በማለትም፡ ለሚያስፈልገን፡ እርዳታም፡ እንጠይቀዋለን።

፬ ጸሎታችንንም፡ "በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፣ አሜን፡" በማለት፡ በአዳኛችን፡ ስም፡ አንዘጋለን።

ጸሎታችን፡ ሁልጊዜም፡ እነዚህን፡ አራት፡ ደረጃዎችን፡ መከተል፡ የለበትም፣ ነገር፡ ግን፡ እነዚህ፡ በእዕምሮአችን፡ ውስጥ፡ ካሉ፡ ጸሎት፡ ለማድረግ፡ ዘንድ፡ እንድንማር፡ ይረዱናል። ጸሎታችንን፡ ሁልጊዜም፡ በመጀመሪያው፡ እና፡ በመጨረሻው፡ ደረጃዎች፡ መጀመርና፡ መጨረስ፡ አለብን፣ በመሀል፡ የምንለው፡ ግን፡ ምን፡ አስፈላጊ፡ ነው፡ ብለን፡ በምናስበው፡ ይወሰናል። አንዳንድ፡ ጊዜም፡ አብዛኛውን፡ ጸሎታችንን፡ የሰማዩ፡ አባታችንን፡ በማመስገን፡ ማሳለፍ፡ እንፈልግ፡ ይሆናል። በሌሎች፡ ጊዜ፡ ግን፣ አብዛኛውን፡ ጸሎታችንን፡ የእርሱን፡ እርዳታ፡ በመጠየቀ፡ ማሳለፍ፡ እንፈልግ፡ ይሆናል።



### የግል፡ ጸሎቶች

እያንዳንዱ፡ ሰው፡ ቢያንስ፡ በእያንዳንዱ፡ ጠዋት፡ እና፡ ማታ፡ በግል፡ መጸለይ፡ ይገባዋል። ወላጆችም፡ ልጆቻቸው፡ መናገር፡ ሲጀምሩ፡ የግል፡ ጸሎት፡ እንዲያቀርቡ፡ ማስተማርም፡ ይገባቸዋል። ወላጆችም፡ ከልጆቻቸው፡ ጋር፡ ተንበርክከው፡ የጸለዩትን፡ እያንዳንዱን፡ ዓረፍት፡ ነገር ከእነርሱ፡ በኋላ፤ እንዲደግሙ፡ በማድረግ፡ እንዴት፡ እንደሚጸልዩ፡ ማስተማርም፡ ይችላሉ። ብዙም፡ ሳይቆዩ፣ ልጆች፡ የራሳቸውን፡ ጸሎት፡ ማድረግ፡ ይችላሉ።

## የቤተሰብ፡ ጸሎቶች

እያንዳንዱ፡ ቤተሰብ፡ በየቀኑ፡ እንደቤተሰብ፡ ይጸልዩ። ቤተሰቡ፡ በሙሉ፡ ተንበርክከው፣ እና፡ የቤተሰቡ፡ መሪ፡ ጸሎትን፡ ያቅርቡ፡ ወይም፡ አንድ፡ የቤተሰብ፡ አባል፡ ጸሎቱን፡ እንዲያቀርቡ፡ ይጠይቁ። እያንዳንዱም፡ የቤትሰብ፡ አባል፡ ጸሎት፡ የማቅረብ፡ መደበኛ፡ እድል፡ ሊኖራቸው፡ ይገባል። ትንንሽ፡ ልጆችም፡ ወላጆቻቸው፡ እየረዷቸው፡ በተራቸው፡ መጸለይም፡ ይችላሉ። የቤተሰቡ፡ ጸሎት፡ ክፍለ፡ ጊዜ፡ ልጆችን፡ እንዴት፡ እንደሚጸልዮ፡ እና፡ እንደ፡ እግዚአብሔር፡ ማመን፣ ትህትና፣ እና፡ ፍቅር፡ አይነት፡ መሰረቶችን፡ የሚያስተምሩት፡ እጅግ፡ ጥሩ፡ ጊዜ፡ ነው።



## ልዩ፡ ጸሎቶች

እግዚአብሔር፡ ጸሎታቸውን፡ ሁልጊዜም፡ ለማዳመጥ፡ የተዘጋጀ፡ እንደሆነ፡ ወላጆች፡ ልጆቻቸውን፡ ማስተማር፡ ይገባቸዋል። ከግል፤ እና፡ ከቤተሰብ፡ ጸሎቶች፡ በተጨማሪም፣ የተለየ፡ እርዳታ፡ ወይም፡ ምስጋናን፡ ለመግለፅ፡ ሲፈልጉ፡ በማንኛውም፡ ጊዜ፡ መጸለይ፡ ይችላሉ።

## ምግብን፡ መባረክ



ወላጆች፡ የቤተሰቦቻቸው፡ አባላት፡ እግዚአብሔርን፡ ለምግባቸው፡ እንዲያመሰግኑ፡ እና፡ ከመመገባቸው፡ በፊት፡ ምግቡን፡ እንዲባርከው፡ እንዲጠይቁ፡ ስለመማራቸው፡ ማጤን፡ ይገባቸዋል። ልጆችም፡ ጨምሮ፣ እያንዳንዱም፡ ሰው፡ በተራ፡ ጸሎት፡ ማቅረብ፡ ይገባቸዋል። ምግብን፡ ለመባረክ፡ መጸለይ፡ ወላጆች፡ እና፡ ልጆች፡ ለሰማዩ፡ አባታችን፡ ምስጋና፡ ለማቅረብ፡ እንዲማሩ፡ ይረዳል።

# የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት

የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት፡ በቅርብ፡ ለተጋቡትም፣ ልጆች፡ ላሏቸው፡ አባትና፡



እናትም፣ ልጆቻቸውን፡ ካለባለቤተ፡ ለሚያሳድጉትም፣ ልጆቻቸው፡ እቤት፡ ለማይኖሩት፡ ወላጆችም፣ በቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት፡ ቡድን፡ አባል፡ ለሆኑ፡ ወጣት፡ ሰዎችም፣ እና፡ በብቻቸው፡ ወይም፡ ከጓደኛ፡ ጋር፡ አብረው፡ ለሚኖሩት፡ በሙሉ፡ ነው። ጉዳያቸው፡ ምንም፡ ቢሆንም፣ የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽትን፡ የሚያደርጉ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይባረካሉ። ቤተክርስትያን፡ ቤተሰቦች፡ ለቤተሰብ፤ የቤት፡ ምሽት፡ በአንድ፡ ላይ፡ መሆን፤ ይችሉ፡ ዘንድ፡ ሰኞ፡ ምሽቶችን፡ ከሌሎች፡ የቤተክርስትያን፤ ስራዎች ነጻ፡ አድርጋለች።

የቀዳሚ፡ አመራር፡ እንዲህ፤ ብለዋል፡ “የጌታን፡ ምክር፡ ተከትላችሁ፡ እና፡ መደበኛ፡ የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽቶችን፡ ካደረጋችሁ፡ ታላላቅ፡ በረከቶች፡ እንደምታገኙ፡ ቃል፡ እንገባላችኋለን። በቤተክርስትያን፡ ያሉ፡ ወላጆች፡ ለልጆቻቸው፡ የወንጌል፡ መሰረትን፡ እንዲያስተምሩ፡ እና፡ ምሳሌ፡ እንዲሆኑ፡ ያለባቸውን፡ ሀላፊነት፡ እንዲቀበሉ፡ ያለማቋረጥ፡ እንጸልያለን። በዚህ፡ ታላቅ፡ አስፈላጊ፡ ሀላፊነት፡ ላይ፡ የተጋችሁ፡ ትሆኑ፡ ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ ይባርካችሁ።” (“Message from the First Presidency,” *Family Home Evening Resource Book* [1983], iv)

የቤተሰብ፡ ፓትሪያርክ፡ በመሆኑ፣ አባት፡ የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽትን፡ ይመራል። አባት፡ በቤት፡ ውስጥ፡ ከሌለም፣ እናት፡ ትመራለች። ወላጆችም፡ የቤተሰብ፡ የቤት፤ ምሽትን፡ ይመራሉ፡ ወይም፡ አንዱ፡ የቤተስትብ፡ አባል፡ እንዲመራ፡ ይመድባሉ። ትምህርቱንም፡ ያስተምራሉ፡ ወይም፡ እድሜአቸው፡ ለማስተማር፡ ለደረሱት፡ ልጆች፡ የማስተማር፡ ሀላፊነቱን፡ ይመድባሉ። ታዳጊ፡ ልጆችም፡ መዝሙርን፡ በመምራት፣ ቅዱሳት፡ መጻህፍትን፡ በመጥቀስ፣ ስዕሎችን፡ በመያዝ፣ የመዝናኛ፡ ምግብና፡ መጠጥን፡ በማደል፣ እና፡ በመጸለይ፡ ለመርዳትም፡ ይችላሉ።

ለቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት፡ የቀረበ፡ ቅድመ፡ ተከተል፡ የሚከተሉት፡ ናቸው፤

- የመክፈቻ፡ መዝሙር፡ (በቤተሰቡ)
- የመክፈቻ፡ ጸሎት፡ (በአንድ፡ የቤተሰብ፡ አባል)
- የግጥም፡ ወይም፡ የቅዱሳት፡ መጻህፍት፡ ንባብ፡ (በአንድ፡ የቤተሰብ፡ አባል)
- ትምህርት (በአባት፣ እናት፣ ወይም፡ እድሜው፡ በደረሰ፡ አንድ፡ ልጅ)
- ተሳትፎ (በአንድ፡ የቤተሰብ፡ አባል፡ መሪነት፡ ሁሉም፡ የቤተሰብ፡ አባሎች፡ እየተሳተፉ)
- የመዝጊያ፡ መዝሙር (በቤተሰቡ)
- የመዝጊያ፡ ጸሎት (በአንድ፡ የቤተሰቡ፡ አባል)
- የመዝናኛ፡ ምግብ፡ እና፡ መጠጥ

ቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽታቸውን፡ በተለያዩ፡ መንገዶች፡ ማድረግ፡ ይችላሉ። ቤተሰብን፡ የሚያቀራርብ፣ ለእርስ፡ በራሳቸው፡ ያላቸውን፡ ፍቅር፡ የሚያጠናክር፣ ወደ፡ ሰማዩ፡ አባታቸው፡ ይበልጥ፡ የሚያቀርባቸው፣ እና፡ በጻድቅነት፡ እንዲኖሩ፡ የሚያበረታታቸው፡ ማንኛውም፡ ተሳትፎ፡ የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት፡ ይሆናል። ቅዱሳት፡ መጻህፍትን፡ ማንበብ፣ ወንጌልን፡ መወያያት፣ ምስክርን፡ መካፈል፣ የአገልግሎት፡ ፕሮጀክቶችን፡

መካፈል፣ የአገልግሎት፡ ፕሮጀክቶችን፡ ማከናወን፣ በአንድ፡ ላይ፡ መዘመር፣ ለሽርሽር፡ መሄድ፣ የቤተሰብ፡ ጨዋታ፡ መጫወት፣ እና፡ የእግር፡ ጉዞ፡ ማድረግ፡ የተሳትፎ፡ ምሳሌዎች፡ ናቸው። ሁሉም፡ የቤተሰብ፡ የቤት፡ የምሽቶች፡ ጸሎትን፡ ማካተት፡ አለባቸው።

የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት፡ ትምህርቶች፡ ቅዱሳት፡ መጻህፍት፤ በተለይም፡ ከጠቅላላ፡ ጉባኤ፡ ንግግር፡ የመጡ፡ የኋለኛው፡ ቀን፡ ቅዱሳን፡ ነብያት፡ ትምህርቶች፤ እናም፡ የግል፡ ኣጋጣሚዎች፡ እና፡ ምስክሮች፡ ላይ፡ ሊመረኮዝ፡ ይችላል። ብዙዎቹ፡ ትምህርቶች፡ በአዳኝ፡ ልደት፣ ሕይወት፡ ትምህርቶች፣ እና፡ ኃጥያት፡ ክፍያ፡ ላይ፡ ማተኮር፡ ይገባቸዋል። የወንጌል፡ መሰረቶች፣ የወንጌል፡ መርሆዎች፣ ለእምነት፡ እውነታዊነት፣ እና፡ ለወጣቶች፡ ጥንካሬ፡ በሚባሉት፡ መፅሐፎች፡ እናም፡ የቤተክርስትያኑ፡ መፅሔቶች፡ ውስጥ፡ ያሉት፡ መረጃዎች፡ እና፡ ሌሎች፡ ፅሁፎች፡ የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት፡ ትምህርት፡ ክፍል፡ የሚሆኑ፡ ብዙ፡ ርዕሶች፡ የሚይዙ፡ ናቸው።

ለቤት፡ ምሽት፡ የመወያያ፡ አርዕስቶች፡ እንደሚከተሉት፡ ናቸው፤

- የደህንነት፡ እቅድ
- የኢየሱስ፡ ሕይወትና፡ ትምህርቶች
- ንስሀ፡ መግባት
- ጸሎት
- ጾም
- የጥበብ፡ ቃል
- የጌታ፡ የግብረ፡ ገብነት፡ መስፈርቶች
- የቅዱስ፡ ቁርባን፡ ትርጉም
- አስራት
- ምስጋና
- ታማኝነት
- ለእግዚአብሔር፡ አምልኮት፡ እና፡ ለፍጥረቶቹም፡ አክብሮት
- ለጥምቀት፣ ለክህነት፡ ስልጣን፤ ሹመት፣ ወይም፡ ለጋብቻ፡ መዘጋጀት
- ቤተመቅደስ፡ ውስጥ፡ ለመግባት፡ መዘጋጀት
- ቅዱሳት፡ መጻህፍትን፡ ማንበብ
- ሰንበትን፡ በቅድስና፡ መጠበቅ
- ሌሎችን፡ ይቅር፡ ማለት
- ምስክር፡ ማግኘት፡ እና፡ መካፈል
- ከሌሎች፡ ጋር፡ ወንጌልን፡ መካፈል
- የቤተሰብ፡ ታሪኮችን፡ መሰብሰብ
- ሞትን፡ መረዳትና፡ መቀበል
- የቤተሰብን፡ ችግር፡ መፍታት
- የቤተሰብን፡ ገንዘብ፡ ማስተዳደር
- የቤተሰብ፡ የቤት፡ ስራን፡ መከፋፈል
- ሙዚቃን፡ ማድነቅና፡ መደሰት

## በዓላት፡ እና፡ ልዩ፡ ጊዜዎች

እንደ፡ ገና፣ ፋሲካ፤ የክህነት፡ ስልጣን፡ ደግሞ፡ መመለስ፡ ክብረ፡ በዓል፤ ጉባኤ፤ የቤትሰብ፡ አባል፡ በሚስዮን፡ መሄድ፤ ወይም፡ የቤተሰብ፡ አባል፡ መወለድ፣ መጠመቅ፣ ወይም፡ መሾም፡ አይነት፡ የበዓል፡ ቀናት፡ እና፡ ልዩ፡ ጊዜዎችም፡ የወንጌሉን፡ እውነቶች፡ የማስተማር፡ ጥሩ፡ እድሎች፡ ሊሆኑም፤ ይችላሉ።

# አስራት፡ እና፡ በኩራቶች



ጌታ፡ ሕዝቦቹን፡ በአስራት፡ ህግ፡ እንዲኖሩ፡ እና፡ ቃል፡ ለተገባላቸው፡ በረከቶች፡ ብቁ፡ እንዲሆኑ፡ አዟል። **(ሚልክያስ 3፡8–11) ይመልከቱ)**

ወላጆች፡ ልጆቻቸውን፡ የአስራትን፡ ህግ፡ እና፡ በኩራትን፡ የሚያስተምሩባቸው፡ ጥሩ፡ ጊዜ፡ ቢኖር፡ የእራሳቸውን፡ በሚከፍሉበት፡ ወቅት፡ ነው። ልጆች፡ ወላጆቻቸው፤ ሲያደርጉ፡ በሚያዩት፡ ነገሮች፡ ይሳባሉ። የኪስ፡ ገንዘብ፡ የሚቀበሉ፡ ልጆች፡ ከላዩ፡ አስራት፡ መክፈል፡ ይገባቸዋል። እያንዳንዱ፡ ልጆች፡ ሶስት፡ የገንዘብ፡ ማጠራቀሚያ፡ ሊኖራቸው፡ ይችላሉ፤ አንድ፡ ለአስራት፣ አንድ፡ ለሚስዮን፣ እና አንድ፡ ለወጪ። ልጆች፡ ገንዘብ፡ በተቀበሉም፡ ጊዜ፣ በመጀመሪያ፡ 10፡ ፐርሰንቱን፡ በአስራት፡ ማጠራቀሚያቸው፡ ውስጥ፡ ማስገባት፣ ከዚያም፡ የተወሰነ፡ ገንዘብን፡ ለሚስዮን፡ ማጠራቀሚያ፡ ውስጥ፡ ጨምረው፣ የቀረውን፡ በወጪ፡ ማጠራቀሚያ፡ ውስጥ፡ ማስቀመጥን፡ መማር፡ ይገባቸዋል።

ልጆች፤ አስራት፡ ሲከፍሉ፣ ወላጆች፡ የአስራት፡ መክፈያ፡ ቅፅን፡ እንዲሞሉ፣ ገንዘቡን፡ በኤንቨሎፕ፡ ውስጥ፡ እንዲከቱ፣ እና፡ ኤጲስ፡ ቆጶስ፡ አመራር፡ ወይም፡ ለቅርንጫፍ፡ አስተዳደር፡ ኤንቨሎፑን፡ እንዲሰጡ፡ ወይም፡ እንዲልኩ፡ ማስተማርም፡ ይገባቸዋል።

## የምግብ፡ ሰዓት፡ ውይይቶች

የምግብ፡ ሰዓቶች፡ ስለወንጌል፡ ለመወያየት፡ አመቺ፡ ጊዜዎች፡ ሊሆኑ፡ ይችላሉ። ትንንሽ፡ ልጆች፡ የወንጌል፡ ጥያቄዎች፡ መጠየቅና፡ መመለስ፡ ይወዳሉ። መልሶቹን፡ በማያውቁ፡ ጊዜ፣አባትየው፡ ወይም፤ እናትየው፡ አጭር፡ መልሶች፡ መስጠት፡ እና፡ ወንጌልን፡ ማስተማር፡ ይችላሉ። ሁሉም፡ የምግብ፡ ሰዓቶች፡ የወንጌል፡ ውይይቶችን፡ ማካተት፡ የለባቸውም፣ ነገር፡ ግን፡ በሳምንት፡ ሁለት፡ ወይም፡ ሶስት፡ እንደዚህ፡ አይነት፡ ውይይቶችን፡ በማድረግ፡ ወንጌልን፡ ቤተሰቦች፡ እንዲማሩ፡ ይረዳቸዋል።

## የመኝታ፡ ጊዜ፡ ታሪኮች

ብዙ፡ ልጆች፡ የመኝታ፡ ሰዓት፡ ታሪኮችን፡ ስለሚወዱ፣ ከቅዱስ፡ መጻህፍቶች፣ የቤተክርስትያን፡ ህትመቶች፣ ወይም፡ ከግል፡ አጋጣሚዎች፡ ውስጥ፡ ታሪኮችን፡ ማንበብ፡ ወይም፡ መንገር፡ ጥሩ፡ ወንጌል፡ የማስተማሪያ፡ እድሎችን፡ ያቀርባሉ። ስለታማኝነት፣ ስለመካፈል፣ እና፡ ስለደግነት፡ ታሪኮችም፡ አስፈላጊ፡ የወንጌል፡ መሰረቶችን፡ ያስተምራሉ።

## በአንድነት፡ መስራት

ወንጌሉን፡ የማስተማር፡ አጋጣሚዎች፡ የሚመጡበት፡ ብዙ፡ ጊዜዎችንም፡ ቤተሰቦች፡ አብረው፡ በቤት፡ አካባቢ፡ በሚሰሩበት፡ ወቅት፡ ይፈጥራሉ። ለምሳሌ፣ ቤትን፡



በሚያጸዱበት፡ ወይም፡ በጓሮ፡ ወይም፡ በአትክልት፡ ስፍራ፡ ውስጥ፡ በሚሰሩበት፡ ጊዜ፣ ወላጆች፡ ስለ፡ ወንጌል፡ የሚያወሩባቸውን፡ አጋጣሚዎች፡ በንቃት፡ መጠባበቅ፡ ይገባቸዋል። ልጅ፡ በአብዛኛው፡ ጥያቄዎች፡ ይጠይቃሉ። ወላጆችም፡ ቀላል፡ መልሶች፡ ለመስጠትም፡ ጊዜአቸውን፡ ለመውሰድ፡ ይገባቸዋል። “ግሩም፡ ሰራተኛ፡ ነህ። የሰማዩ፡ አባት፡ እንደሚኮራብህም፡ እርግጣኛ፡ ነኝ፡” ወይም፡ የሰማዩ፡ አባት፡ የሰራቸው፡ ውብ፡ ደመናዎችን፡ ተመልከት፡ የሚሉትን፡ አስተያየቶች፡ መስጠት፡ ልጆችን፡ ለሰማዩ፡ አባት፡ ምስጋና፡ እንዲኖራቸው፡ የሚያደርግ፡ ስሜትና፡ እርሱ፡ እውነታዊ፡ እንደሆነ፡ ማረጋገጫ፡ ይሰጣቸዋል።

## የቤተሰብ፡ ሸንጎ



ወላጆች፡ የቤተሰብ፡ አባሎቻቸውን፡ በቤተሰብ፡ ሸንጎ፡ ለመጥራት፡ ይችላሉ። የቤተሰብን፡ አላማ፡ ለማውጣት፣ የቤተሰብ፡ ችግሮችን፡ ለመፍታት፣ ስለ፤ ገንዘብ፡ ለመወያየት፣ እቅድ፡ ለመስራት፣ እርስ፡ በራስ፡ ለመደጋገፍ፡ እና፡ ለመጠናከር፣ ምስክሮችን፡ ለማካፈል፣ እና፡ ለእርስ፡ በራሳቸው፡ ለመጸለይ፡ ቤተሰቦች፡ ይህን፡ የሸንጎ፡ ጊዜ፡ መጠቀም፡ ይችላሉ። ሸንጎው፡ አስፈላጊ፡ በሆነበት፡ ጊዜ፡ ሊከናወን፡ ይቻላል። ወላጆች፡ የቤተሰብ፡ ሸንጎን፡ በየእሁድ፡ ወይም፡ ከቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት፡ ጋት፡ ሊያያይዙት፡ ይችላሉ። ለሌሎች፡ አስተያየቶች፡ እና፡ ስሜቶች፡ አክብሮት፡ መስጠት፡ ለቤተሰብ፡ ሸንጎዎች፡ በጣም፡ አስፈላጊ፡ ነው።

## የግል፤ ቃል፡ ጥያቄ



ልጆቻቸውን፡ ወደ፡ እነርሱ፡ ለማቅረብ፣ ለማበረታታት፣ እና፡ ወንጌሉን፡ ለማስተማር፡ ብዙ፡ ወላጆች፡ ከእያንዳንዱ፡ ልጆች፡ ጋር፡ መደበኛ፤ የግል፡ ቃል፡ ጥያቄ፡ ያደርጋሉ። እንደነዚህ፡ አይነት፡ ቃል፡ ጥያቄዎች፡

በአብዛኛው፡ ጊዜ፡ መደበኛ፡ የሆነም፡ ያልሆነም፡ ሊሆን፡ ይችላል፣ በየጊዜውም፡ መደረግ፡ ይቻላል።

ወላጆች፡ በልጃቸው፡ ላይ፡ ያላቸውን፡ ፍቅር፡ እና፡ እምነት፡ መግለጽ፡ ይገባቸዋል፣ እናም፡ ልጆችም፡ ስለ፡ ማንኛውም፡ ጉዳይ፣ ችግር፣ ወይም፡ አጋጣሚ፡ የእርሱን፡ ወይም፡ የእርሷን፡ ስሜታ፡ ለመግለፅ፡ እድል፡ ማግኘትም፡ ይገባቸዋል። ወላጆችም፡ በጥንቃቄ፡ ማዳመጥ፡ እና፡ የልጅን፡ ችግር፡ እና፡ ሚስጥርን፡ በጠና፡ መቀበልም፡ ይገባቸዋል። ወላጅ፡ እና፡ ልጅም፡ አብረው፡ ለመጸለይም፡ ሊፈልጉ፡ ይችላሉ። ሌሎች፡ የቤተሰብ፡ አባሎችን፡ የሚያካትቱ፡ በቃል፡ ጥያቄ፡ ውስጥ፡ የሚፈጠሩት፡ ችግሮችንም፡ በሚቀጥለው፡ በየቤት፡ የቤት፡ ምሽት፡ ውስጥ፡ ሊወያዩበትም፡ ይቻላል።

## የቤተሰብ፡ ተሳትፎዎች

ከቤተስብ፡ በሙሉ፡ ጋር፡ የሚያሳልፉበትን፡ ጊዜ፡ ወላጆች፡ ማቀድ፡ ይገባቸዋል። ሽርሽሮች፣ የመዝናኛ፤ ስፍራዎች፡ ዘንድ፡ መጓዝ፣ የቤተሰብ፡ የስራ፡ እቅድ፣ የቤት፡ ውስጥ፡ እና፡ የጓሮ፡ ስራ፣ ዋና፣ የእግር፡ ጉዞ፡ ሽርሽር፣ እናም፡ ጥሩ፡ ፊልሞችና፡ ሌሎች፡ መዝናኛዎች፡ ቤተሰቦች፡ አብረው፡ ለመሳተፍ፡ ከሚችሏቸው፡ ነገሮች፡ ውስጥ፡ ጥቂቶቹ፡ ናቸው።

ተሳትፎዎችን፡ አብረው፡ የሚደሰቱ፡ ቤተሰብ፡ ታላቅ፡ ፍቅርና፡ እርስ፡ በእርስ፡ መስማማት፡ ይሰማቸዋል። ልጆችም፡ ወደ፡ ወላጆቻቸው፡ ቅርበት፡ ሲሰማቸው፣ ወላጆቻቸውን፡ ለማዳመጥ፡ እና፡ የእነርሱን፡ ምክር፤ ለመከተል፡ ፍቃደኛም፡ ይሆናሉ። ወላጆችም፡ ወንጌልን፡ በውጤታማነት፡ ለማስተማርም፡ ይችላሉ።



# የቤተሰብ፡ ሀላፊነትን፡ ማሟላት



ሁሉም፡ ሰዎችን፡ ወደ፡ ክርስቶስ፡ እንዲመጡ፡ መርዳት፡ የጌታ፡ ቤተክርስትያን፡ አላማ፡ ነው። ቤተሰቦችም፡ የሚቀጥሉትን፡ በማድረግ፡ ይህን፡ አላማ፡ ለማከናወን፡ ይችላሉ፤

፩ የእራሳቸው፡ መንፈሳዊ፡ እና፡ ስጋዊ፡ ፍላጎት፡ ማሟላት፡ እና፡ የሌሎችን፡ ፍላጎቶች፡ እንዲሳኩ፡ መርዳት።

፪ ወንጌልን፡ ከሌሎች፡ ጋር፡ መካፈል።

፫ የቤተሰብ፡ አባሎች፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ ስነ፡ ስርዓቶችን፡ እንዲፈፅሙ፡ ማረጋገጥ፡ እና፡ ይህን፡ በረከቶች፡ ሳያገኙ፡ ለሞቱት፡ ቅድመ፡ አያቶቻቸውም፡ የዚህን፡ ስርዓት፡ በረከቶች፡ እንዲያገኙ፡ መርዳት።

## መንፈሳዊ፡ እና፡ ስጋዊ፡ ፍላጎቶች

### መንፈሳዊ፡ ፍላጎቶች

"ወንጌልን፡ በቤት፡ ውስጥ፡ ማስተማር፡" የሚለው፡ የዚህ፡ መፅሀፍ፡ ቅድመ፡ ክፍል፣ ቤተሰቦች፡ እንዴት፡ መንፈሳዊ፡ ፍላጎቶችን፡ ለሟሟላት፡ እንደሚችሉ፡ መረጃዎችን፡ ሰጥቷል።

### ስጋዊ፡ ፍላጎቶች

ቤተሰቦች፡ የራሳቸውን፡ ስጋዊ፡ ፍላጎት፡ ለሟሟላት፡ እና፡ ሌሎችንም፡ ለመርዳት፡ እራሳቸውን፡ የቻሉ፡ መሆን፡ አለባቸው። ራስን፡ ለመቻል፣ የቤተሰብ፡ አባሎች፡ ለመስራት፡ ፈቃደኞች፡ መሆን፡ አለባቸው። ስራም፡ የአካላዊ፣ የአዕምሯዊ፣ እና፡ መንፈሳዊ፡ ጥረት፡ ነው። የብልፅግና፣ የየደስታ፣ የራስ፡ ክብር፣ እና፡ ስኬታማነትም፡

ምንጭ፡ ነው። ወላጆች፡ ራሳቸውን፡ ችለው፡ በተመሳሳይም፡ ልጆቻቸውን፡ እንደእነርሱ፡ እንዲሆኑ፡ ማስተማር፡ ይገባቸዋል። ራስ፡ መቻል፡ ችግረጮችን፡ እንዲረዱ፡ ያስችላቸዋል።

አባቶች፡ ለቤተሰቦቻቸው፡ የህይወት፡ መሰረታዊ፡ ፍላጎቶች፡ እና፡ እንክብካቤ፡ ለቤተሰቦቻቸው፡ የማቅረብ፡ ሀላፊነት፡ አለባቸው። የእናቶች፡ የመጀመሪያ፡ ሀላፊነትም፡ ልጆችን፡ በጥንቃቄ፡ ማሳደግ፡ ነው። ወላጆች፡ ቤተሰቡ፡ የጸዳ፡ ቤት፣ ጥሩ፡ ምግብ፣ ልብሶች፣ የተሟላ፡ ህክምና፡ እና፡ የጥርስ፡ ህክምን፡ እንክብካቤ፣ የመማር፡ እድሎች፣ ገንዘብን፡ በስርዓት፡ የመጠቀም፡ መመሪያ፣ እናም፡ ከተቻለም፡ የእራሳቸውን፡ ምግብ፡ የሚያሳድጉበት፡ ስልጠና፡ ማግኘታቸውን፡ ማረጋገጥ፡ አለባቸው። ወላጆች፡ ልጆቻቸውን፡ እንዴት፡ ምግባቸውን፡ እንደሚያዘጋጁ፡ እና፡ ለበኋላ፡ ጥቅም፡ ምግቡን፡ እንዴት፡ ሳይበላሽ፡ ማስቀመጥ፡ እንደሚችሉም፡ ማስተማር፡ ይገባቸዋል።

ወላጆች፡ እነዚህ፡ ስጋዊ፡ ፍላጎቶችን፡ ለማሟላት፡ ጠንክረው፡ ለመስራት፡ ፍቃደኛ፡ መሆን፡ ይገባቸዋል።“እናም፡ ልጆቻችሁ፡ ተርበው፡ አለበለዚያም፡ ተራቁተው፡ እንዲሄዱ፡ አትፈቅዱም።” (ሞዛያ 4:14) ወላጆች፡ በህመም፣ አደጋ፣ ከስራ፡ መውጣት፣ ወይም፡ ሌሎች፡ ችግሮች፡ በሚደርሱበት፡ ጊዜ፡ የቤተሰቦቻቸው፡ መሰረታዊ፡ ፍላጎቶችን፡ ለሟሟላት፡ መዘጋጀት፡ እና፡ ማቀድ፡ አለባቸው። አባት፡ የቤተሰቡ፡ ስጋዊ፡ ፍላጎቶችን፡ ለማሟላት፡ ካልቻለ፡ እና፡ ሌሎች፡ የቤተሰብ፡ አባላት፡ መርዳት፡ ካልቻሉ፣ ከካህናት፡ መሪዎች፡ እርዳታ፡ መጠየቅ፡ ይችላል።

ልጆችም፡ ወላጆቻቸውን፡ በስራ፡ በማገዝ፣ ትምህርታቸውን፡ በስርዓት፡ በመከታተል፣ ልብሶቻቸውን፡ እና፡ ሌሎች፡ ንብረቶቻቸውን፡ በመንከባከብ፣ እራሳቸውን፡ እና፡ ቤታቸውን፡ በማጽዳት፣ እና፡ ጤንነታቸውን፡ በመጠበቅ፡ የቤተሰባቸውን፡ ስጋዊ፡ ፍላጎት፡ ለማሟላት፡ ለመርዳት፡ ይችላሉ።

የቤተሰብ፡ አባላት፡ የመጻፍ፣ የማንበብ፣ እና፡ መሰረታዊ፡ የሂሳብ፡ ስለቶችን፡ የመቀመር፡ ችሎታቸውን፡ ማሻሻል፣ እናም፡ ዕውቀታቸውን፡ ለማዳበር፡ እና፡ ችሎታቸውን፡ ለማሻሻል፡ የሚረዱ፡ ማናቸውንም፡ አጋጣሚዎች፡ መጠቀም፡ ይገባቸዋል። የጥበብ፡ ቃል፡ አክብረው፡ ለጤና፡ ተስማሚ፡ ምግቦችን፡ መመገብ፡ አለባቸው። በሚቻልበትም፡ ቦታ፡ ሁሉ፣ ቤተሰቦች፡ የአመት፡ ቀለብ፡ ማስቀመጥ፣ ወይም፡ የሚቻለውን፡ ያህል፣ ህይወትን፡ ለማቆየት፡ የሚያስችል፡ ነገሮችን፡ ማከማቸት፡ ይገባቸዋል። አስፈላጊ፡ ያልሆኑ፡ እዳዎችን፡ ማስወደግ፣ ለወደፊትም፡ ገንዘብ፡ መቆጠብ፣ ሀላፊነታቸውን፡ መፈጸም፣ እና፡ ያላቸውን፡ ሀብትም፡ በስርዓት፡ በመጠቀም፡ ገንዘብን፡ ማባከን፡ ማስወገድ፡ አለባቸው።

ወላጆች፡ ልጆቻቸውን፡ ከሌሎች፡ ጋር፡ ተካፍለው፡ እንዲኖሩ፡ ማስተምር፡ ይገባቸዋል። ምንም፡ እንኳን፡ ትንሽ፡ ሀብት፡ ቢኖራቸውም፣ ማንኛውም፡ አንዳንድ፡ ነገሮች፡ መስጠት፡ ይችላሉ። ችግረኞችን፡ መርዳት፡ የሚቻልበት፡ አንድ፡ መንገድ፡ ቢኖር፡ በየወሩ፡ በመጾም፡ እና፡ የተራቡትን፡ ለመመገብ፣ ቤት፡ የሌላቸውን፡ መጠለያ፡ ለመስጠት፣ ለታረዙት፡ ለማልበስ፣ እና፡ የሚሰቃዩትን፡ ስቃያቸውን፡ ለማስታገስ፡ ጥቅም፡ ላይ፡ የሚውለውን፡ በኩራቶችን፡ መስጠት፡ ነው። ሌሎችን፡

ለታረዙት፡ ለማልበስ፣ እና፡ የሚሰቃዩትን፡ ስቃያቸውን፡ ለማስታገስ፡ ጥቅም፡ ላይ፡ የሚውለውን፡ በኩራቶችን፡ መስጠት፡ ነው። ሌሎችን፡ ስንረዳ፣ ለጌታ፡ ያለንን፡ ፍቅር፡ እናሳያለን። “ከእነዚህ፡ አነስተኛ፡ ከሆኑት፡ ወንድሞቼ፡ ለአንዱ፡ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንድዳደጋችሁት፡ ነው።” (ማቴዎስ 25፡40)

## ወንጌልን፡ መካፈል



ጌታ፣ በኋለኛው፡ ቀን፡ ነብያቱ፡ በኩል፣ እያንዳንዱ፡ የቤተክርስትያን፡ አባላት፡ ከሌሎች፡ ጋር፡ ወንጌልን፡ የመካፈል፡ ሀላፊነት፡ እናዳላቸው፡ አስተምሯል። “እንዲጠነቀቅ፡ የተነገረው፡ ጎረቤቱን፡ የማስጠናቀቅ፡ ሀላፊነት፡ አለው።” (ትምህርት፡ እና፡ ቃልኪዳን 88፡81) የመፅሐፈ፡ ሞርሞን፡ ነብይ፡ አልማ፡ እንደገለጸው፣ ስንጠመቅ፡ “በሁሉም፡ ጊዜ፡ በሁሉም፡ ነገር፡ የእግዚአብሔር ምስክር፡ በመሆን፡” ለመቆም፡ ፈቃደኛ፡ መሆን፡ ይገባናል። (ሞዛያ 18፡9)

የቤተሴብ፡ አባላት፡ ዘመዶቻቸው፣ ጋደኞቻቸው፣ እናም፡ ጎረቤቶቻቸው፡ ስለ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወንጌል፡ እና፡ ምን፡ አይነት፡ በረከቶች፡ በህይወታቸው፡ እንደሚያመጣላቸው፡ እንዲማሩ፡ ለመርዳት፡ የሚችሉትን፡ ሁሉ፡ ማድረግ፡ አለባቸው። ወንጌልን፡ በመካፈል፣ ወላጆች፡ እና፡ ልጆች፡ የእራሳቸውን፡ ምስክሮች፡ ያጠናክራሉ፣ እናም፡ ወደሌሎችም፡ የወንጌሉን፡ በረከቶችም፡ ያስገኛሉ። ቤተሰቦች፡ የሚቀጥሉትን፡ ማድረግ፡ ይችላሉ፤

- ትእዛዛትን፡ ሁሉ፡ በማክበር፡ ጥሩ፡ ምሳሌ፡ መሆን። (ማቴዎስ፡ 5፡16ን፡ ተመልከቱ)
- ለቤተክርስትያን፡ አባልነት፡ አመስጋኝ፡ መሆን፡ እና፡ ሌሎች፡ ሰዎች፡ እነርሱ፡ አባል፡ እንደሆኑ፡ ማሳወቅ። (ሮሜ 1፡16ን፡ ተመልከቱ)
- በቅርብ፡ የሚያውቋቸውን፡ ሰዎች፡ ስለ፡ ቤተክርስትያኑ፡ ለማወቅ፡ እንደሚፈልጉ፡ መጠየቅ።
- ወንጌሉን፡ ለመስማት፡ የተዘጋጀ፡ አንድ፡ ቤተሰብን፡ ወይም፡ ግለሰብን፡ ለመምረጥ፡ እንዲረዳቸው፡ ጌታን፡ መጠየቅ።
- ወደ፡ የቤተሰብ፡ የቤት፡ ምሽት፡ ወይም፡ ወደ፡ ቤተክርስትያን፡ ስብሰባ፡ ወይም፡ ተሳትፎ፡ አብረዋቸው፡ እንዲሄዱ፡ በመጋበዝ፣ የሚያነቡት፡ የቤተክርስትያን፡ መፅሐፎች፡ ወይም፡ በራሪ፡ ወረቀቶችን፡ ለእነርሱ፡ በመስጠት፣ ወይም፡ ስለ፡ ወንጌሉ፡ በረተከቶች፡ እነርሱን፡ በማነጋገር፡ አይነት፡ መንገዶች፡ ቤተሰቡን፡ ወይም፤ ግለሰቡን፡ ከቤተክርስትያኑ፡ ጋር፡ ማስተዋወቅ።
- ቤተሰቡን፡ ወይም፡ ግለሰቡን፡ ከሚስዮናውያን፡ እንድማሩ፡ በቤታቸው፡ መጋበዝ።

ወላጆች፡ የሙሉ፡ ጊዜ፡ ሚስዮንን፡ ለማገልገል፡ እራሳቸውን፡ እና፡ ልጆቻቸውን፡ የማዘጋጀት፡

ሀላፊነት፡ አለባቸው። ልጆችን፣ በልዩም፡ ወንድ፡ ልጆችን፣ ለማዘጋጀት፣ ወላጆች፡ ወንጌልን፡ በቤት፡ ማስተማር፣ የግል፡ እና፡ የቤተሰብ፡ ቅዱሳት፡ መጻህፍት፡ ጥናት፡ እና፡ ጸሎት፡ ማድረግ፣ እናም፡ ስለ፡ ወንጌሉ፡ መካፈል፡ ሀላፊነቶች፡ እና፡ በረከቶች፡ በየጊዜው፡ መወያየት፡ ይገባቸዋል።

## ለሚኖሩት፡ እና፡ ለሙታን፡ የሚፈጸሙ፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ ስነ፡ ስርዓቶች



በቤተ፡ መቅደስ፡ ውስጥ፡ ብቁ፡ የቤተክርስትያን፡ አባላት፡ የተቀደሱ፡ ስነ፡ ስርዓቶችን፡ ተቀብለው፡ ከእግዚአብሔር፡ ጋር፡ ቃል፡ ኪዳን፡ ይገባሉ። እነርሱም፡ ለሞቱት፡ ቅድመ፡ አያቶች፡ የስነ፡ ስርዓቶችን፡ ስራ፡ ለማከናወን፡ ይሰራሉ። በሚቻልበትም፡ ቦታ፣ አባት፡ እና፡ እናት፡ ከክህነት፡ መሪዎቻቸው፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ መግቢያ፡ ፈቃድ፡ መቀበል፡ እና፡ ወደ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ በመሄድ፡ የግላቸውን፡ ስነ፡ ስርዓት፡ ለመፈጸም፡ ይገባቸዋል። ወደ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ለመሄድ፡ የማይችሉ፡ ከሆነም፣ ለቤተ፡ መቅደስ፡ መግቢያ፡ ፈቃድም፡ ብቁ፡ ሆነው፡ መኖርም፡ ይገባቸዋል።

ቤተሰቦች፡ ከመቀባላቸው፡ በፊት፡ ለሞቱት፤ ቅድመ፡ አያቶቻቸው፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ ስርዓቶች፡ የመፈጸም፡ ቅዱስ፡ ሀላፊነት፡ አለባቸው። የግል፡ ስነ፡ ስርዓታቸውን፡ የፈጸሙ፡ ሰዎችም፣ የቤተ፡ መቅደስ፡ በአካባቢያቸው፡ መገኘት፡ እና፡ ችሎታ፡ በሚፈቅድላቸው፡ ሁኔታ፡ በየጊዜው፡ ወደ፡ ቤተ፡ መቅደሱ፡ በመመለስ፡ ለሞቱት፡ ቅድመ፡ አያቶቻቸው፡ ስነ፡ ስርዓቶችን፡ መፈጸም፡ ይገባቸዋል።

አባቶች፡ እና፡ እናቶች፡ የበረከቶች፣ የጥምቀቶች፣ የሹመቶች፣ የጋብቻዎች፣ የሚኞችን፡ ሰርተፊኬቶች፤ ጠቃሚ፡ ደብዳቤዎች፤ ፎቶግራፎች፤ ከጋዜጦች፡ ላይ፡ ተቀደው፡ የወጡ፡ ፅሁፎች፣ እና፡ ተመሳሳይ፡ ቁሳቁሶችን፡ ጨምረው፡ በእነርሱ፡ እና፡ በልጆቻቸው፡ ህይወቶች፡ ውስጥ፡ የሚገኙትን፡ ክስተቶች፡ የያዙ፡ መረጃዎችን፡ ማሰባሰብ፡ ይገባቸዋል። የራሳቸውን፡ የግል፡ ታሪኮችን፡ አቀናብረው፡ ማስቀመጥ፡ እና፡ እያንዳንዱ፡ የቤተሰብ፡ አባል፡ የግል፡ ታሪኩን፡ ጠብቆ፡ እንዲያስቀምጥ፡ ማበረታታት፡ ይገባቸዋል። በእድሜያቸው፡ አነስ፡ ያሉትን፡ ልጆች፡ የግላቸውን፡ ታሪኮች፡ መጻፍ፡ እንዲጀምሩ፡ መረዳት፡ ይገባቸዋል።

ቤተሰቦች፡ የዘሮቻቸውን፡ መረጃ፡ ማሰባሰብ፡ እና፡ በቤተሰብ፡ ታሪክ፡ ውስጥ፡ ማስፈር፡ አለባቸው። ለእነርሱ፡ በጣም፡ ቅርብ፡ የሆኑትን፡ የአራት፡ ትውልዶች፡ መረጃ፡ በማቀናበር፡ ይጀምሩ።

# የመምራት፡ ሥልጣን



በስቴክ፧ በሚስዮን፧ ወይም፡ በዲስትሪክት፡ አመራር፡ ስር፧ የክህነት፡ ስልጣን፡ ቡድን፡ እና፡ የድጋፍ፡ ሰጪ፡ መሪዎች፡ ወላጆች፡ የሶስቱን፡ የቤተሰብ፡ መሰራትዊ፡ ሀላፊነቶቻቸው፡ እንዲገባቸው፡ እና፡ እንዲፈፅሙ፡ ማስተማር፡ ይገባቸዋል። (በገፅ፡ **14–17** ይመልከቱ) መሪዎችም፡ አባት፡ እና፡ አናቶችን፡ እንዴት፡ ቤተሰቦቻቸውን፡ እንደሚመሩም፡ ማስተማር፡ ይገባቸዋል። ቤተሰቦችም፡ በተነጠለ፡ ቦታ፡ ከኖሩም፧ የስቴክ፧ ሚስዮን፧ ወይም፡ የዲስትሪክት፡ መሪዎችም፡ ወላጆች፡ ሀላፊነታቸውን፡ እንዲማሩ፡ እና፡ እያሟሉ፡ እንደሆኑ፡ ማረጋገጥ፡ አለባቸው።

# በቤት፡ ውስጥ፡ ለአምልኮት፡ ስርዓት፡ መሰብሰብ (በተነጠለ፡ ቦታ፡ ለሚኖሩ፡ ቤተሰቦች)



አንዳንድ፡ ቤተሰቦች፡ በተነጠለ፡ ቦታ፡ ስለሚኖሩ፡ ለዎርድ፡ ወይም፡ ለቅርንጫፍ፡ ስብሰባዎች፡ ሁልጊዜም፡ ተሳታፊ፡ ለመሆን፡ አይችሉም። በስቴክ፣ በሚስዮን፣ ወይም፡ በዲስትሪክት፡ አመራር፡ ፍቃድ፡ በኩል፣ እንደነዚህ፡ አይነት፡ ቤተሰቦች፡ የሰንበት፡ አምልኮን፡ በቤታቸው፡ ውስጥ፡ ማድረግ፡ ይገባቸዋል። በአካባቢያቸው፡ የተመሰረተ፡ ቤተክርስትያን፡ ከሌለም፣ ቤተሰቦች፡ የአካባቢ፡ አመራር፡ ፈቃድን፡ ማግኘት፡ አለባቸው።

አባት፡ ወይም፡ ሌላ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ ያዢ፡ ብቁ፡ ከሆነ፣ በአሮናዊ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ ውስጥ፡ ቄስ፡ ከሆነ፡ ወይም፡ የመልከጼዴቅ፡ ክህነት፡ ስልጣን፡ ካለው፣ እና፡ ከክህነት፡ ስልጣን፡ መሪዎቹ፡ ፍቃድ፡ ካለው፣ ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ አዘጋጅቶ፡ መባረክ፡ ይችላል። የክህነት፡ ስልጣን፡ የያዘ፡ ማንም፡ ሰው፡ ቅዱስ፡ ቁርባኑን፡ ማስተላለፍ፡ ይችላል። ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ አገልግሎት፡ መስጫ፡ መመሪያዎች፡ በዚህ፡ መፅሐፍ፡ ገጽ፡ 25–26 ውስጥ፡ ይገኛሉ።

የሰንበት፡ አምልኮ፡ ስርዓት፡ ቀለል፡ ያለ፣ አምልኮን፡ የሚያሳይ፡ እና፡ ክብርን፡ የሚሰጥ፡ መሆን፡ አለበት። የሚቀጥሉትንም፡ ሊይዝ፡ ይችላል፡

፩ የመክፈቻ፡ መዝሙር

፪ የመክፈቻ፡ ጸሎት

፫ ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ መባረክ፡ እና፡ ማስተላለፍ

፬ ከሚቀጥሉት፡ ውስጥ፡ አንድ፡ ወይም፡ ሁለት፡ ነገሮች፡

- አንድ፡ ወይም፡ ሁለት፡ አጭር፡ ንግግሮች፡ ወይም፡ ምስክርነቶች

- እንደ፡ ቤተሰብ፡ የቅዱስ፡ መጻህፍትን፡ ማንበብ፡ እና፡ መወያየት
- በአንድ፡ የቤተሰብ፡ አባል፡ በኩል፡ የሚሰጥ፡ ትምህርት

፫ የመዝጊያ፡ መዝሙር

፬ የመዝጊያ፡ ጸሎት

የሰንበት፡ አምልኮ፡ ስርዓትን፡ ሲያቅዱ፣ ወላጆች፡ የጌታን፡ መንፈስ፡ መመሪያ፡ መፈለግ፡ እናም፡ መከተል፡ ይገባቸዋል። የመፅሐፈ፡ ሞርሞን፡ ህዝቦች፡ ስለዚህ፡ አይነት፡ ስርዓት፡ ምሳሌ፡ ሰጥተዋል፡ “እናም፡ ጉባኤዎቻቸው፡ በቤተክርስቲያኗ፡ በመንፈስ፡ ስራዎች፡ እናም፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ኃይል፡ ይመራል፤ የመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ኃይልም፡ እንዲሰብኩ፣ ወይም፡ እንዲያስጠነቅቁ፣ ወይም፡ እንዲፀልዩ፣ ወደጌታ፡ እንዲማፀኑ፡ ወይም፡ እንዲዘምሩ፡ ይመራቸዋል።” (መሮናይ 6:9)

ቤተሰብ፡ ቅዱሳት፡ መፅሐፍትን፡ መሰረታዊ፡ መመሪያቸው፡ ማድረግም፡ ይገባዋል። በተጨማሪም፣ የአጠቃላይ፡ ጉባኤ፡ ንግግሮችን፣ የወንጌል፡ መሰረቶችን፣ የወንጌል፡ መርሆችን፣ ለእምነት፡ እውነታዊነትን፣ ለወጣቶች፡ ጥንካሬን፣ የሚስዮን፡ በራሪ፡ ወረቀቶችን፣ የቤተክርስትያን፡ መፅሔቶችን፣ እና፡ ሌሎች፡ የቤተክርስትያን፡ ህትመቶችን፡ እና፡ የድምፅና፡ ምስል፡ መረጃዎችን፡ መጠቀምም፡ ይችላሉ።

አግባብ፡ ያለው፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ በቤተሰቡ፡ ውስጥ፡ የያዘ፡ ሰው፡ ከሌለም፣ አባት፡ ወይም፡ እናት፡ አብረው፡ መዝሙር፡ መዘመር፣ ቅዱሳት፡ መፅሐፍትን፡ ማንበብ፣ መጸለይ፡ እናም፡ ወደ፡ እርስ፡ በራሳቸው፡ እና፡ ወደ፡ ሰማዩ፡ አባታ፡ ይበልጥ፡ መቅረብም፡ እንዲችሉ፡ ቤተሰብን፡ ይሰብሰቡ። የቤተሰብ፡ የተመደበ፡ የክህነት፡ መሪም፡ ቤተሰቡ፡ ቅዱስ፡ ቁርባን፡ ለመቀበል፡ የሚችሉበት፡ እድልም፡ ማዘጋጀት፡ ይገባቸዋል።

ወላጆች፡ የእግር፡ ጉዞዎች፣ ሽርሽሮች፣ ጥሩ፡ ፊልሞች፣ የዘመድ፡ ጉብኝቶች፣ ስፖርቶች፣ የሙዚቃ፡ ፕሮግራሞች፡ እና፡ ዋና፡ የመሳሰሉ፤ ሳምንታዊ፡ ተሳትፎዎችንም፡ ማዘጋጀት፡ ይገባቸዋል።

ቤተሰብም፡ አስራትን፣ የጾም፡ በኩራቶችን፣ እና ሌሎች፡ መዋጮችን፡ ለእነርሱ፡ ለተመደቡት፡ የክህነት፡ መሪዎች፡ ይስጡ።

ቤተሰብ፡ ለቤተክርስትያኑ፤ የፅሁፍ፡ ሪፖርት፡ አያቀርቡም፣ ነገር፡ ግን፡ የተመደበው፡ የክህነት፡ መሪ፡ ፡ በየጊዜው፡ ስለቤተሰቡ፡ ሁኔታና፡ ደህንነት፡ ሪፖርት፡ እንዲያቀርብ፡ ከአባትየው፡ ጋር፡ ቃል፡ ጥያቄዎች፡ ማደረግ፡ ይገባዋል። አስፈላጊም፡ ከሆነ፣ መሪዎች፡ በስልክ፡ ቃል፡ ጥያቄውን፡ መፈጸም፡ ይችላሉ።

# የክህነት፡ ስርዓቶች፡ እና፡ በረከቶች



የክህነት፡ ስርዓቶች፡ በክህነት፡ ስልጣን፡ የሚከናወኑ፡ በጌታ፡ የተሰጡ፡ ቅዱስ፡ ተግባራት፡ ናቸው። የክህነት፡ በረከቶች፡ በክህነት፡ ስልጣን፡ በኩል፡ ለመፈወስ፣ ለማፅናናት፣ እና፡ ለማበረታታት፡ የሚሰጡ፡ ናቸው። እነዚህን፡ ስርዓቶች፡ እና፡ በረከቶች፡ የሚፈፅሙ፡ ወንድሞችም፡ በወንጌሉ፡ መሰረት፡ በመኖር፤ እና፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ለመመራት፡ በመጣር፡ እራሳቸውን፡ ማዘጋጀት፡ አለባቸው። እያንዳንዱን፡ ስርዓቶች፡ እና፡ በረከቶች፡ ክብርን፡ በሚሰጥ፡ መልክ፡ መፈጸም፡ እና፡ ከሚከተሉት፡ መስፈርቶች፡ ጋር፡ መጣጣም፡ ይገባቸዋል፤

፩ ስርዓቶች፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፤ ስም፡ መፈጸም፡ አለባቸው።

፪ ስርዓቶች፡ በክህነት፡ ስልጣን፡ መፈጸም፡ አለባቸው።

፫ ስርዓቶች፡ ለስርዓቱ፡ ማስፈጸሚያ፡ የተወሰኑበትን፡ ቃል፡ በመጠቀም፡ ወይም፡ ቅብዓ፡ ቅዱስን፡ በመጠቀም፡ አይነት፡ በመሳሰሉት፡ አስፈላጊ፡ ቅድመ፡ ተከተል፡ መፈጸም፡ አለባቸው።

፬ አስፈላጊ፡ ከሆነም፣ ስርዓቶች፡ ትክክለኛውን፡ ቁልፍ፡ የያዙ፡ የክህነት፡ መሪ፡ መፍቀድም፡ አለባቸው። የክህነት፡ መሪ፡ ፈቃድ፡ የሚያስፈልጋቸው፡ ስርዓቶች፡ ለልጆች፡ ስም፡ ማውጣት፡ እና፡ በረከቶችን፡ መስጠት፣ ጥምቀቶችን፡ እና፡ ማረጋገጫዎችን፡ መፈጸም፣ የክህነት፡ ስልጣንን፡ መስጠት፡ እና፡ በክህነት፡ ሀላፊነት፡ መሾም፣ ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ መባረክ፡ እና፡ ማስተላለፍ፣ እናም፡ መቃብሮችን፡ መባረክ፡ ናቸው።

*ስርዓቶችን፡ ወይም፡ በረከቶችን፡ ለማከናወን፡ ብዙ፡ ወንድሞች፡ የሚሳተፉ፡ ከሆኑ፣ እያንዳንዱ፡ የግራ፡ እጁን፡ በግራው፡ በኩል፡ ላይ፡ በቆመው፡ በሌላው፡ ወንድም፡ ትከሻ፡ ላይ፡ ያሳርፍ። ብዙ፡ የክህነት፡ ባለስልጣኖችን፡ የመጋበዝ፡ ልምድም፡ ይወገድ።*

በዚህ፡ ክፍል፡ ውስጥ፡ የተገለጹት፡ ስርዓቶች፡ እና፡ በረከቶች፡ አባቶችን፡ ለቤተሰቦቻቸው፡ እንደ፡ ፓትሪያርክ፡ እንዲያገለግሉ፡ ይረዷቸዋል።

## ለልጆች፡ ስም፡ ማውጣት፡ እና፡ በረከት፡ መስጠት



“ልጆች፡ ያሏቸው፡ እያንዳንዱ፡ የክርስቶስ፡ ቤተክርስትያን፡ አባሎች፡ ልጆቻቸውን፡ በቤተክርስትያኑ፡ ፊት፡ ወደ፡ ካህናት፡ በማምጣት፣ ካህናቱም፡ እጆቻቸውን፡ በክርስቶስ፡ ስም፡ ልጆቹ፡ ላይ፡ አሳርፈው፣ እናም፡ በእርሱ፡ ስም፡ መባረክ፡ አለባቸው።” (ትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን 20:70) ይህን፡ ራዕይ፡ በመከተል፣ ለልጆች፡ ስም፡ ለማውጣት፡ እና፡ በረከት፡ ለመስጠት፡ የመልከጼዴቅ፡ ክህነት፡ ስልጣን፡ የያዙ፡ ብቁ፡ ወንዶች፡ ብቻ፡ መካፈል፡ ይችላሉ። *ለልጆች፡ ስም፡ የማውጣት፡ እና፡ በረከት፡ የመስጠት፡ ስርዓት፡ የአመራር፡ ባለስልጣን፡ ፈቃድ፡ ያስፈልገዋል።*

ህጻን፡ በሚባረክ፡ ጊዜ፡ የመከጼዴቅ፡ ክህነት፡ ስልጣን፡ ያላቸው፡ ወንዶች፡ ክብ፡ ሰርተው፡ ህጻኑን፡ በእጃቸው፡ ይይዛሉ። እድሜው፡ ከፋ፡ ያለው፡ ልጅ፡ በሚባረክበት፡ ጊዜ፣ ወንዶች፡ እጆቻቸውን፡ በልጁ፡ ጭንቅላት፡ ላይ፡ ላላ፡ አድርገው፡ ይጭናሉ። በረከቱን፡ የሚሰጠውም፡ ሰው፡-

፩ የሰማዩ፡ አባት፡ ስምን፡ ይጠራ።

፪ በረከቱ፡ በመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ በኩል፡ እንደሆነ፡ ይገልጻል።

፫ ልጅን፡ ስም፡ ይሰጣል።

፬ *መንፈስ፡* እንደሚመራም፡ የክህነት፡ በረከት፡ ይሰጣል።

፭ በኢየሱስ፡ ክርስቶች፡ ስምም፡ ይዘጋል።



## ጥምቀት

*በአስተዳዳሪው፡ ባለስልጣን፡ አመራር፡ በኩል፣* ብቁ፡ ቄስ፡ ወይም፡ የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ ያለው፡ ወንድ፡ ሰው፡ ጥምቀትን፡ መፈጸም፡ ይችላል። ይህን፡ ለማድረግም፣ እርሱ፡

፭ ከሚጠመቀው፤ ሰው፡ ጋር፡ በውሀ፡ ውስጥ፡ ይቆማል።

፮ ለጥንቃቄ፡ እና፡ ለምቾት፣ የሚጠመቀውን፡ ሰው፡ ቀኝ፡ እጅ፡ በግራ፡ እጁ፡ ይይዛል፤ የሚጠመቀውም፡ ሰው፡ የሚያጠምቀውን፡ ሰው፡ ግራ፡ እጅ፡ በግራ፡ እጁ፡ ወይም፡ እጁን፡ ይይዛሉ።

፯ ቀኝ፡ እጁን፡ በአራት፡ ማዕዘን፡ ቅርፅ፡ ያነሳል።

፰ የሰውየውን፡ ሙሉ፡ ስም፡ በመግለፅ፣ "በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በተሰጠኝ፡ ሀላፊነት፣ በአብ፡ በወልድ፣ እና፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ አጠምቅሀለሁ፡" ይበል። (ትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን 20፡73)

፱ ተጠማቂውን፡ እፍንጫውን፤ ወይም፡ አፍንጫዋን፡ ለምቾት፡ በቀኝ፡ እጃቸው፤ እንዲይዙ፡ ያድርግ፤ የሚያጠምቀውም፣ ሰው፡ የቀኝ፡ እጁን፡ በሰውየው፡ ጀርባ፡ ላይ፡ አስቀምጦ፡ ሰውየውን፣ ልብሱንም፡ ጨምሮ፣ ሙሉ፡ በሙሉ፡ ውሀ፡ ውስጥ፡ ያጠልቀዋል።

፲ ሰውየውን፡ ከውሀ፡ ውስጥ፡ እንዲወጣ፡ ይረዳዋል።

ሁለት፡ ቄሶች፡ ወይም፡ የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ ያላቸው፡ ሰዎች፡ እያንዳንዱን፡ ጥምቀት፡ በትክክል፡ እንደተፈጸሙ፡ ለማረጋገጥ፡ ምስክር፡ ይሁኑ። በትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን፡ 20፡73፡ ላይ፡ ያሉት፡ የጥምቀት፡ ቃላቶቹ፡ በትክክል፡ ካለተባሉ፡ ወይም፡ የሰውየው፡ሰውነት፡ ወይም፡ ልብሶች፡ በሙሉ፡ በውሀ፡ ውስጥ፡ ካልጠለቁ፣ ጥምቀቱ፡ መደገም፡ አለበት። አጥማቂው፡ እና፡ ተጠማቂው፡ እርጥብ፡ ሲሆኑ፡ ገላ፡ የማያሳዩ፡ ነጭ፡ ልብሶች፡ መልበስ፡ ይገባቸዋል።

## የአባልነት፡ ማረጋገጫ

ወላጆቻቸው፡ የቤተክርስትያን፡ አባል፡ ያልሆኑ፡ ስምንት፡ አመት፡ እድሜ፡ ያላቸው፡



ወይም፡ ዘጠኝ፡ አመት፡ ወይም፡ ከዚያ፡ በላይ፡ የሆኑ፡ ተቀያሪዎች፡ በቅዱስ፡ ቁርባን፡ ስብሰባ፡ ጊዜ፡ በአባልነት፡ ይረጋገጣሉ። (ትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን፡ 20፡41ን፡ ተመልከቱ) ከወላጆቻቸው፡ አንዱ፡ በአካባቢው፡ ከተገኙ፡ እና፡ ሁለቱም፡ ወላጆቻቸው፡ ለጥምቀቱ፡ እና፡ ለአባልነት፡ መረጋገጫ፡ ፈቃድ፡ ከሰጡ፣ የስምንት፡ አመት፡ ልጆች፡ ከተጠመቁ፡ በኋላ፡ ወዲያው፡ አባልነታቸው፡ መረጋገጥ፡ ይቻላል። በኤጲስ፡ ቆጶስ፡ ወይም፡ በቅርንጫፍ፡ ፕሬዘደንት፡ መሪነት፡ በኩል፣ አንድ፡ ወይም፡ ከዚያ፡ በላይ፡ የመልከጼዴቅ፤ የክህነት፡ ስልጣን፡ ያላቸው፡ ወንዶች፡ ይህን፡ ስርዓት፡ መፈጸም፡ ይችላሉ። እጆቻቸውን፡ በሰውየው፡ ጭንቅላት፡ ላይ፡ ላላ፡አድርገው ይጭናሉ። ይህን፡ ስርዓት፡ የሚፈጽመውም፡ ሰው፤

፩ የሰውየውን፡ ሙሉ፡ ስም፡ ይገልጻል።

፪ ስርዓቱ፡ የሚፈጸመው፡ በመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ በኩል፡ እንደሆነ፡ ይገልጻል።

፫ ሰውየውን፡ እንደ፡ የኋለኛው፡ ቀን፡ ቅዱሳን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በተክርስትያን፡ አባል፡ ያረጋግጣል።

፬ "መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ተቀበል፡" በማለት፡ የመንፈስ፡ ቅዱስን፡ ስጦታ፡ ይሰጣል።

፭ መንፈስ፡ እንደሚመራም፡ የክህነት፡ በረከት፡ ይሰጣል።

፮ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ይዘጋል።

## የክህነት፡ ስልጣንን፡ መስጠት፡ እና፡ በክህነት፡ ሀላፊነት፡ መሾም



*ኤጲስ፡ ቆጶስ፡ ወይም፡ የቅርንጫፍ፡ ፕሬዘደንት፡ የአሮናዊ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ መሰጠትን፡ እና፡ ለዲያቆን፣ አስተማሪ፣* እና፡ ቄስ፡ ሀላፊነት፡ መሾምን፡ ይቆጣጠራሉ። በአሮናዊ፡ የክህነትስ፡ ስልጣን፡ ሀላፊነት፡ ሰው፡ ከመሾሙ፡ በፊት፣ ከኤጲስ፡ ቆጶስ፡ ወይም፡ ከቅርንጫፍ፡ ፕሬዘደንት፡ ጋር፡ ቃል፡ ንግግር፡ ማድረግ፡ እና፡ ብቁ፡ ሆኑ፡ መገኘት፡ አለበት። በተጨማሪም፣ በቅዱስ፡ ቁርባን፡ ስብሰባ፡ ውስጥ፡ ድጋፍ፡ ማግኘትም፡ አለበት። በኤጲስ፡ ቆጶስ፡ ወይም፡ በቅርንጫፍ፡ ፕሬዘደንት፡ አመራር፡ በኩል፣ ቄስ፡ የኤሮናዊ፡ የክህነት፡ ስልጣንን፡ ሰጥቶ፡ በአሮናዊ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ ሀላፊነትም፡ መሾም፡ ይችላል።

*የስቴክ፡ ወይም፡ የሚስዮን፡ ፕሬዘደንት፡ የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ መሰጠትን፡ እና፡ ወደካህን፡ እና፡ ሊቀካህን፡ ሀላፊነት፡ መሾምን፡ ይቀጣጠራሉ።*

የክህነት፡ ስልጣንን፡ ለመስጠት፡ ወይም፡ ለክህነት፡ ስልጣን፡ ሀላፊነት፡ ለመሾም፣ አስፈላጊውን፡ የክህነት፡ ስልጣን፤ ያላቸው፡ አንድ፡ ወይም፡ ከዚያ፡ በላይ፡ ሰዎች፡ እና፡ በአስተዳዳሪው፡ ባለስልጣን፡ ፈቃድ፡ በኩል፡ እጆቻቸውን፡ በሰውየው፡ ጭንቅላት፡ ላይ፡ ላላ፡ በማድረግ ይጭናሉ። ስርዓቱን፡ የሚፈጽመው፡ ሰው፤

፩ ሰውየውን፡ በሙሉ፡ ስሙ፡ ይጠራዋል።

፪ ስርዓቱ፡ የሚፈጸምበትን፡ ስልጣንን፡ (የአሮናዊ፡ ወይም፡ የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን) ይገልጻል።

፫ ከዚህ፡ በፊት፡ ቀድሞ፡ የተሰጠ፡ ካልሆነ፣ አሮናዊ፡ ወይም፡ የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣንን፡ ይሰጣል።

፬ ሰውየውን፡ በአሮናዊ፡ ወይም፡ በመልከጼዴቅ፡ ይክህነት፡ ስልጣን፡ ሀላፊነት፡ ውስጥ፡ ይሾማል፡ እናም፡ በሀላፊነቱ፡ ያሉትን፡ መብቶች፣ ሀይሎች፣ እና፡ ስልጣኖችንም፡ ይሰጠዋል።

፫ መንፈስ፡ እንደሚመራው፡ የክህነት፡ በረከት፡ ይሰጣል።

፬ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ይዘጋል።

## ቅዱስ፡ ቁርባን



ቅዱስ፡ ቁርባን፡ በጣም፡ የተቀደሰ፡ ስርዓት፡ ነው። ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ መካፈል፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ህይወት፡ ትምህርቶች፣ እና፡ ኃጥያት፡ ክፍያን፡ ለማስታወስ፡ እድል፡ ይሰጣል። በጥምቀት፡ ወቅት፡ ከጌታ፡ ጋር፡ የተገባውን፡ ቃል፡ ኪዳን፡ የማሳደሻ፡ ጊዜ፡ ነው። (ሞዛያ 18፡8–10ን፡ ተመልከቱ)

አስተማሪዎች፡ እና፡ ቄሶች፡ ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ ማዘጋጀት፡ ይችላሉ፤ ቄሶችም፡ ይባርኩታል፤ እና፡ ዲያቆኖች፣ አስተማሪዎች፣ እና፡ ቄሶችም፡ ያስተላልፉታል። የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ ያላቸው፡ ወንድሞችም፡ ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ ማዘጋጀት፣ መባረክ፡ እና፡ ማስተላለፍ፡ ይችላሉ፣ ነገር፡ ግን፡ በተለምዶ፡ ይህን፡ የሚያደርጉት፡ የሚገኙት፡ አሮናዊ፡ ክህነት፡ ባለስልጣን፡ ወንድሞች፡ ቁጥር፡ በጣም፡ ጥቂት፡ ሲሆን፡ ብቻ፡ ነው። ሰው፡ በጣም፡ ከፍተኛ፡ ኃጥያት፡ ከፈጸመ፣ ንስሀ፡ እስኪገባ፡ እና፡ ጉዳዩን፡ ከኤጲስ፡ ቆጶስ፡ ወይም፡ ከቅርንጫፍ፡ ፕሬዘደንት፡ ጋር፡ መፍትሄ፡ እስኪያገኝ፡ ድረስ፡ ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ ማዘጋጀት፣ መባረክ፡ እና፡ ማስተላለፍ፡ አይገባውም።

ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ የሚያዘጋጁት፣ የሚባርኩት፡ እና፡ የሚያስተላልፉት፡ ይህን፡ ስርዓት፡ ለሌሎች፡ የሚፈፅሙት፡ በጌታ፡ ፋንታ፡ ነው። የክህነት፡ ስልጣን፡ ያላቸው፡ እያንዳንዱ፡ ሰዎች፡ ይህን፡ ሀላፊነት፡ በክብር፡ እና፡ ፈሪሀ፡ እግዚአብሔር፡ በሞላበት፡ አመለካከት፡ መፈጸም፡ ይገባቸዋል። ንጹ፡ በሆነ፣ በጥሩ፡ አቀራረብ፣ እና፡ በመልካም፡ አለባበስ፡ መዘጋጀትም፡ ይገባዋል። የግል፡ አቀራረብም፡ የስርዓቱን፡ ቅድስና፡ ማንጸባረቅ፡ ይገባዋል።

ቅዱስ፡ ቁርባንን፡ የሚያዘጋጁት፡ ወንድሞችም፡ ይህን፡ ስብሰባ፡ ከመጀመሩ፡ በፊት፡ ማዘጋጀት፡ ይገባቸዋል። ያልተቆረሰውን፡ ዳቦውን፡ በንጹህ፡ የዳቦ፡ ትሪው፡ ላይ፡ እና፡ ውሀ፡ የያዙ፡ የቅዱስ፡ ቁርባን፡ ሲኒዎችን፡ በቅዱስ፡ ቁርባን፡ ጠረጴዛው፡ ላይ፡ ያስቀምጡ። ዳቦ፡ እና፤ ውሀውንም፡ በንጹህ፣ ነጭ፡ ጨርቅም፡ ይሸፍኑት።

በቅዱስ፡ ቁርባን፡ መዝሙር፡ ወቅትም፣ በቅዱስ፡ ቁርባን፡ ጠርጴዛ፡ አጠገብ፡ ያሉት፡ ጨርቁን፡ ከዳቦ፡ ትሪው፡ ላይ፡ ገልጠው፡ ዳቦውን፤ በትናንሹ፡ ይቆራርጡ። ከመዝሙሩ፡ በኋላ፣ ዳቦውን፡ የሚባርከው፡ ሰው፡ ተንበርክኮ፡ የዳቦውን፡ የቅዱስ፡ ቁርባን፡ ጸሎት፡ ያቅርብ። ከዚያም፡ ወንድሞች፡ ዳቦውን፡ በአክብሮት፡ እና፡ በስርዓት፡ ለተገኙት፡ ሰዎች፡ ያስተላልፉ። በስብሰባው፡ ላይ፤ ያለው፡ የአመራሩ፡ ባለስልጣን፡ ቅዱስ፡ ቁርባኑን፡ በመጀመሪያ፡ ይቀበል። በስብሰባው፡ ላይ፤ የተገኙት፡ ሁሉ፤ ቁርባኑን፤ የመካፈል፡ እድል፡ ካገኙ፡ በኋላ፣ ቅዱስ፡

ቁርባንን፤ የሚያስተላልፉት፡ ትሪዎቻቸውን፡ ወደ፡ ቅዱስ፡ ቁርባን፡ ጠረጴዛ፡ ይመልሱ። ቅዱስ፡ ቁርባኑን፡ የሚባርኩትም፡ ዳቦው፡ እንደተላለፈ፡ ወዲያው፡ ትሪዎቹን፡ ይሸፍኑ።

በቅዱስ፡ ቁርባን፡ ጠርጴዛ፡ አጠገብ፡ ያሉት፡ ጨርቁን፡ ከውሀ፡ ትሪዎች፡ ላይ፡ ይግለጡ። ውሀውን፡ የሚባርከው፡ ሰው፡ ተንበርክኮ፡ የውሀውን፡ የቅዱስ፡ ቁርባን፡ ጸሎት፡ ያቅርብ። ወንድሞችም፡ ውሀውን፡ በስብሰባው፡ ውስጥ፡ ላሉት፡ ያስተላልፉ። ትሪዎቹን፡ ወደ፡ ቅዱስ፤ ቁርባን፡ ጠረጴዛ፡ ይመልሱ፡ እናም፡ ይሸፍኗቸው። ከዚያም፡ ቅዱስ፡ ቁርባኑን፡ የባረኩት፡ እና፡ ያስተላለፉት፡ ከምዕመናኑ፡ ጋር፡ መቀመጫቸውን፡ ይያዙ።

ቅዱስ፡ ቁርባን፣ ልጆችንም፡ ጨምሮ፣ ለቤተክርስትያን፡ አባላት፡ የሚሰጥ፡ ነው። ስብሰባውን፡ የሚመራው፤ ሰው፡ ቅዱስ፡ ቁርባኑ፡ የሚተላለፈው፡ ለአባሎች፡ ብቻ፡ ነው፡ ብሎ፡ ማስታወቅ፡ የለበትም፤ አባል፡ ያልሆኑትን፡ ቅዱስ፡ ቁርባኑን፡ እንዳይወስዱ፡ ለማገድ፡ የሚደረግ፡ ምንም፡ ነገር፡ የለም።

የቅዱስ፡ ቁርባን፡ ጸሎቶች፡ በግልፅ፣ በትክክል፣ እና፡ በአክብሮት፡ መጸለይ፡ አለባቸው። ቅዱስ፡ ቁርባኑን፡ የሚባርከው፡ ሰው፡ በጸሎቱ፡ ቃላት፡ ላይ፡ ስህተት፡ ካደረገ፡ እና፤ እራሱን፡ መልሶ፡ ካላስተካከለ፣ ኤጲስ፡ ቆጶሱ፡ ወይም፡ የቅርንጫፍ፡ ፕሬዘደንቱ፡ ጸሎቱን፡ ደግሞ፡ በትክክል፡ እንዲያቀርበው፡ ይጠይቁታል።

የዳቦው፡ ጸሎት፡ የሚከተሉት፡ ናቸው፡፡

አቤቱ፡ ዘለዓለማዊ፡ አባት፡ እግዚአብሔር፡ ሆይ፣ ይህንን፡ ዳቦ፡ ለሚበሉት፡ ነፍሳት፡ ሁሉ፡ የልጅህን፡ ስጋ፡ ለማሰብ፡ ይበሉት፡ ዘንድ፤ መንፈሱ፡ ሁልጊዜ፡ ከእነርሱ፡ ጋር፡ ይሆን፡ ዘንድ፤ የልጅህንም፡ ስም፡ በላያቸው፡ ለመውሰድ፡ ፈቃደኞች፡ ይሆኑ፡ ዘንድ፤ እናም፡ ሁልጊዜም፡ እርሱን፡ ሊያስታውሱና፡ የተሰጣቸውንም፡ ትዕዛዛቱን፡ እንዲጠብቁ፡ አቤቱ፡ ለአንተ፡ ለአምላክ፤ ዘለዓለማዊ፡ አባትም፡ ይመሰክሩ፡ ዘንድ፡ በልጅህ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ትባርከው፡ እና፡ ትቀድሰው፡ ዘንድ፡ እንጠይቅሃለን። አሜን። **(ትምህርትና፡ ቃል፡ ኪዳን 20፡77 እና፡ ሞሮናይ 4)**

የውሀ፡ ጸሎት፡ የሚከተለው፡ ነው፡፡

አቤቱ፡ ዘለዓለማዊ፡ አባት፡ እግዚአብሔር፡ ሆይ፣ ይህንን፡ ውሀን፡ ለሚጠጡት፡ ነፍሳት፡ ሁሉ፡ ለእነርሱ፡ ለፈሰሰው፡ ለልጅህ፡ ደም፡ መታሰቢያነት፡ ያደርጉት፡ ዘንድ፤ አቤቱ፡ ዘለዓለማዊ፡ አባት፡ እግዚአብሔር፣ መንፈሱም፡ ከእነርሱ፡ ጋር፡ ይሆን፡ ዘንድ፣ ሁልጊዜም፡ እርሱን፡ በማሰብ፡ ለአንተ፡ ይመሰክሩ፡ ዘንድ፡ እንድትባርከው፡ በልጅህ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ እንጠይቅሃለን። አሜን። **(ትምህርት፡ እና፡ ቃል፡ ኪዳን 20፡79 እና፡ ሞሮናይ 5)**

ቅዱስ፡ ቁርባኑ፡ ወዲያው፤ ስብሰባው፡ እንዳለቀ፡ ወዲያውኑ፡ ከጠርጴዛው፡ ላይ፡ መነሳት፡ ይገባዋል። የቀረው፡ ዳቦም፡ ለምግብነት፡ መጠቀም፡ ይቻላል።

*ቅዱስ፡ ቁርባን፡ የመባረክ፡ እና፡ የማስተላለፍ፡ ስልጣን፡ ከአመራር፡ ባለስልጣን፡ መምጣት፡ ያስፈልገዋል።*

## ቅብዖ፡ ቅዱስን፡ መቀደስ

የታመመ፡ ወይም፡ የሚሰቃይ፡ ሰውን፡ ለመቀባት፡ የተቀደሰ፡ አላማ፡ ያለውን፡ የወይራ፡ ዘይትን፡ አንድ፡ (ወይም፡ ከዚያ፡ በላይ፡) የመልከጼዴክ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ የያዙ፡ ሰዎች፡ ይቀድሱታል። ዘይቱን፡ የሚቀድሰው፡ ሰው፤

፩ የተከፈተ፡ የወይራ፡ ዘይት፡ መያዣን፡ በእጁ፡ ይያዝ።

፪ የሰማዩ፡ አባታችንን፡ ይጥራ።

፫ በመልከጼዴክ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ በኩል፡ ይህን፡ እንደሚፈጽም፡ ይግለፅ።

፬ (መያዣውን፡ ሳይሆን) ዘይቱን፡ ይቀድስ፡ እናም፡ የታመሙትን፡ እና፡ የተሰቃዩትን፡ ለመቀባትም፡ ለይቶ፡ ያስቀምጠው።

፭ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ይዘጋል።



## ለሕሙማን፡ ፈውስ፡ መጸለይ

የመልከጼዴቅ፡ የክህነትስ፡ ስልጣን፡ያላቸው፡ ወንዶች፡ ብቻ፡ ለታመሙት፡ እና፡ ለተሰቃዩት፡ ፈውስ፡ መጸለይ፡ የሚችሉት። በተለምዶ፣ ሁለት፡ ወይም፡ ከዚያ፡ በላይ፡ ለፈወስ፡ መጸለይ፡ ይችላሉ፣ ነገር፡ ግን፡ አንድ፡ ሰው፡ ብቻውንም፡ ሊያደርገው፡ ይችላል።

የመልከጼዴቅ፡ የክህነትስ፡ ስልጣን፡ያለው፡ አባት፡ ለታመሙት፡ የቤተሰብ፡ አባሎቹ፡ ለመፈወስ፡ መጸለይ፡ ይችላል። የመልከጼዴቅ፡ የክህነትስ፡ ስልጣን፡ያላቸው፡ሌላ፡ ሰውን፡ እንዲረዱት፡ መጠየቅም፡ ይችላል።

ለሕሙማን፡ ፈውስ፡ መጸለይ፡ ሁለት፡ ክፍሎች፡ አሉት፤ (፩) በቅብዖ፡ ቅዱስ፡ መቀባት፡ እና፡ (፪) የተቀባውን፡ ማተም።

### በቅብዖ፡ ቅዱስ፡ መቀባት

የመልከጼዴቅ፡ የክህነትስ፡ ስልጣን፡ያለው፡ ሰው፡ የታመመውን፡ ሰው፡ ይቀባል። ይህን፡ ለማድረግም፣ እርሱ፤

፩ ቅብዖ፡ ቅዱስ፡ አንድ፡ ጠብታ፡ በሰውየው፡ ጭንቅላት፡ ላይ፡ ይደርጋል።

፪ በታመመ፡ ሰው፡ ጭንቅላት፡ ላይ፡ እጆቹን፡ ላላ፡ አድርጎ፡ በማስቀመጥ፡ የሰውየውን፡ ወይም፡ የሴትዮዋን፡ ሙሉ፡ ስም፡ ይጠራል።

፫ ሰውየውን፡ የሚቀባው፡ በመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ በኩል፡ እንደሆነ፡ ይገልጻል።

፬ የታመመን፡ እና፡ የሚሰቃይ፡ ሰውን፡ ለመቀባት፡ በተቀደሰ፡ ቅብዖ፡ ቅዱስ፡ እንደሚቀባ፡ ይገልጻል።

፭ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ይዘጋል።

### የተቀባውን፡ ማተም

በተለምዶ፣ ሁለት፡ ወይም፡ ከዚያ፡ በላይ፡ የምልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ የያዙ፡

ወንዶች፡ እጆቻቸውን፡ ላላ፡ አድርገው፡ በታመመው፡ ሰው፡ ጭንቅላት፡ ላይ፡ ያስቀምጣሉ። ከሰዎቹ፡ አንዱ፡ የተቀባውን፡ ያትማል። ይህን፡ ለማድረግ፣ እርሱ፤

፩ ህሙማንን፡ በስሙ፡ ወይም፡ ስሟ፡ ይጠራል።

፪ የተቀባውን፡ የሚያትመው፡ በመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ በኩል፡ እንደሆነ፡ ይገልጻል።

፫ መንፈስ፡ እንደሚመራም፡ የክህነት፡ በረከት፡ ይሰጣል።

፬ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ይዘጋል።

## የአባት፡ በረከቶች፡ እና፡ የመፅናናት፡ እና፡ ለምክር፡ ሌሎች፡ በረከቶች



መንፈስ፡ እንደሚመራው፡ ምሪት፡ እና፡ መፅናኛ፡ለመስጠት፣ የአባት፡ በረከቶች፡ እና፡ የመፅናናት፡ እና፡ የምክር፡ ሌሎች፡ በረከቶች፡ ይሰጣሉ።

በመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ የያዙ፡ አባት፡ ለልጆቻቸው፡ የአባት፡ በረከቶች፡ መስጠት፡ ይችላሉ። እንደነዚህ፡ አይነት፡ በረከቶች፡ ልጆች፡ ለትምህርት፡ ወይም፡ ለሚስዮን፡ ከቤት፡ ወጥተው፡ ሲሄዱ፣ ወይም፡ አዲስ፡ ስራ፡ ሲጀምሩ፣ ሲያገቡ፣ ለወታደርነት፡ አገልግሎት፡ ሲገቡ፣ ወይም፤ ልዩ፡ የግል፡ ችግር፡ ሲያጋጥማቸው፡ በተለይ፡ ይረዱ፡ ይሆናሉ። እነዚህ፡ በረከቶች፡ ለቤተሰብ፡ ታላቅ፡ ጥንካሬ፡ ሊሆኑ፡ ይችላሉ። ቤተሰብ፡ የአባት፡ በረከትን፡ ለቤተሰብ፡ ታሪክ፡ መጻፍ፡ ይችላል፣ ነገር፡ ግን፡ በቤተክርስትያን፡ መዛግብት፡ ውስጥ፡ ተጠብቆ፡ አይቀመጥም። ወላጆች፡ ልጆችን፡ የአባት፡ በረከቶችን፡ በሚያስፈልጋቸው፡ ጊዜ፡ እንዲሹ፡ ማበረታታት፡ ይገባቸዋል።

የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ የያዙ፡ ብቁ፡ ወንዶች፡ የመፅናናት፡ እና፡ የምክር፡ በረከቶችን፡ ለሚስቶቻቸው፣ ለቅርብ፡ ዘመዶቻቸው፣ እና፡ ለጠየቋቸው፡ ሰዎች፡ መስጠትም፡ ይችላሉ።

የአባት፡ በረከቶች፡ ወይም፡ የመፅናናት፡ እና፡ የምክር፡ ሌሎች፡ በረከቶችን፡ ለመስጠት፣ የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ የያዙ፡ ወንዶች፡ እጆቻቸውን፡ ላላ፡ አድርገው፡ በረከቱን፡ በሚቀበለው፡ ሰው፡ ጭንቅላት፡ ላይ፡ ያስቀምጣሉ። ለእነዚህ፡ አይነት፡ በረከቶች፡ ዘይት፡ አያስፈልግም። በረከቱን፡ የሚሰጠውም፡

፩ በረከት፡ የሚቀበሉትን፡ በስሙ፡ ወይም፡ በስሟ፡ ይጠራል።

፪ በመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ በኩል፡ በረከቱን፡ እንደሚሰጥ፡ ይገልጻል።

፫ መንፈስ፡ እንደሚመራም፡ የክህነት፡ በረከት፡ ይሰጣል።

፬ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ይዘጋል።

## መቃብሮችን፡ መባረክ

መቃብሮችን፡ የሚባርክ፡ ሰው፡ የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ ኖሮት፡ በክህነት፡ ባለስልጣን፡ ይህን፡ አገልግሎት፡ ለመምራት፡ ስልጣን፡ መቀበል፤ አለበት።

መቃብርን፡ ለመባረክ፡

፩ የሰማዩን፡ አባት፡ ስምን፡ ይጠራ።

፪ መቃብሩን፡ የሚባርክ፡ በመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ በኩል፡ እንደሆነ፡ ይግለጽ።

፫ የመቅበሪያውን፡ ቦታ፡ እንደ፡ ሬሳው፡ ማረፊያ፡ ቦታ፡ ይባርካል እንዲሁም፡ ይቀድሳል።

፬ ተገቢ፡ ከሆነም፣ እስከ፡ ትንሳኤ፡ ድረስ፡ ቦታው፡ ተቀድሶ፡ ተጠብቆ፡ እንዲቆይም፡ ይጸልይ።

፭ ጌታ፡ ቤተሰብን፡ እንዲያፅናናም፡ ይጠይቃል፡ እናም፡ መንፈስ፡ እንደሚመራውም፡ ሌሎች፡ ሀሳቦችን፡ ይገልጻል።

፮ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ ይዘጋል።

ቤተሰቡ፡ ከፈቀደም፣ ከመቃብር፡ የመባረኪያ፡ ጸሎት፡ ይልቅ፡ የመቃብር፡ ጸሎት፡ አንድ፡ ሰው፡ (የመልከጼዴቅ፡ የክህነት፡ ስልጣን፡ የያዘ፡ ሰው፡ ቢሆን፤ ይመረጣል) ሊያቀርብ፡ ይችላል።

# የቤተክርስትያን፡ እቃዎችን፡ እና፡ ስለቤተሰብ፡ ታሪክ፡ መረጃዎችን፡ (መግለጫዎችን) ማግኘት፡

በአካባቢ፡ የሚገኙት፡ መሪዎች፡ እና፡ ሌሎች፡ አባሎች፡ ቅዱስ፡ መጻህፍቶችን፣ የጥናት፡ ተከታታይ፡ ትምህርቶችን፣ የቤተክርስትያን፡ መፅሔቶችን፣ ልብሶችን፣ እና፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ ልብሶች፡ አይነት፡ የቤተክርስትያን፡ ቁሳቁሶችን፣ ከራሳቸው፡ የቤተክርስትያን፡ ማከፋፈያ፡ ማእከል፡ ወይም፡ አገልግሎት፡ ማእከል፣ ከ Salt Lake Distribution Center፣ ወይም፡ www.lds.org ላይ፡ በሚገኘው፡ በቤተክርስትያን፡ ኦፊሲያላዊ፡ የኢንተርኔ፡ ሳይት፡ ላይ፡ ሊያገኙ፡ ይችላሉ።

ለቤተሰብ፡ ታሪክ፡ ስራ፡ መረጃም፡ www.familysearch.org ላይ፡ በሚገኘው፡ የቤተክርስትያን፡ የቤተሰብ፡ ታሪክ፡ ኢንተርኔት፡ ሳይት፡ ላይ፡ ይገኛል።

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን
የኢየሱስ ክርስቶስ
ቤተክርስቲያን

AMHARIC
4 02311 80506 8
31180 506